የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ
የሕገ መንግሥት ጉዳዮች
አጣሪ ጉባዔ ጽ/ቤት

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ
F.D.R.E. COUNCIL OF CONSTITUTIONAL INQUIRY

The Federal Democratic Republic
Of Ethiopia
Secretariat of
Council of Constitutional Inquiry

ቁጥር
Ref.No. ሕጉን/7438/15/8

ቀን
Date. 11/03/2017

ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የውሳኔ ግልባጭ ስለመስጠት፣

ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ባቀረቡት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መሰረት ጉባዔው ግንቦት 08 ቀን 2016 ዓ/ም ባደረገው ስብሰባ አቤቱታውን ተመልክቶ የቀረበው ጥያቄ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በአብላጫ ድምጽ ውሣኔ የሰጠበትን 33 ገጽ በዚህ ደብዳቤ ሸኚነት እንዲደርስዎ የተደረገ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ
FDRE Council of Constitutional Inquiry

አበበ ታደሰ አበደ
የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ
ጽ/ቤት ምክትል ዋና ዳይሬክተር

ስልክ/Tel: +251 11-1-116888 | ፋክስ/Fax: +251 11 1 ......

መዝገብ ቁጥር 7438/15

ቀን፡- ግንቦት 8/2016 ዓ/ም

**የጉባዔው አባላት፣**

1. ክቡር አቶ ቴዎድሮስ ምህረት..................................ሰብሳቢ
2. ክብርት ወ/ሮ አበባ እምቢአለ ............................ ....ም/ሰብሳቢ
3. የተከበሩ አቶ አማረ ሰጤ........................................አባል
4. የተከበሩ አቶ ገብሬ ኡርጌሶ ....................................አባል
5. የተከበሩ አቶ አብዱረህማን ኢድ-ጣሂር .....................አባል
6. ክብርት ወ/ሮ ደስታ ገብሩ .......................................አባል
7. ክቡር አቶ በሻዳ ገመቹ ...........................................አባል
8. ክቡር አቶ ምትኩ ማዳ.............................................አባል
9. ክቡር አቶ አብዲአዚዝ አህመድ ኑር..........................አባል
10. ክቡር አቶ ቸርነት ሆርዶፋ.......................................አባል
11. ክቡር አቶ ደበበ ኃ/ገብርኤል ...................................አባል

**የሕገ መንግስት ትርጉም አቅራቢ፡-** የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

**አድራሻ፡-** አዲስ አበባ ከተማ

የሰበር ተጠሪዎች 1ኛ) ወ/ሮ ለምለም ግዛው

2ኛ) ብርጉዴ ግዛው

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ በመመርመር የሚከተለውን ውሳኔ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አቅርቧል::

## ክፍል አንድ

### የጉዳዩ አመጣጥ

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 404962 በሆነው ላይ ችሎቱ ለያዘው ጉዳይ እና ሌሎች ሰባት ጉዳዮች እልባት ለመስጠት መሆኑን በመግለጽ በመዝገብ ቁጥር 404962 ላይ በ20/03/2015 ዓ/ም በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት በመላኩ ነው።

በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ተጠሪዎች 1ኛ) ወ/ሮ ለምለም ግዛው፣ 2ኛ) ብርጉዴ ግዛው ከሳሾች በመሆን፣ የሰበር አመልካች አቶ ተስፋዬ ግዛው ተከሳሽ በሆነው በሻሸመኔ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የተጀመረ በሰበር አመልካች እጅ የሚገኝ ኑዛዜ ይሰረዝልን በሚል የቀረበ ክርክር ነው፡፡

የክልሉ ሰበር ተጠሪዎች በ9/11/2013 ዓ/ም ለሻሸመኔ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በሰበር አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ሟች እናታችን ወ/ሮ አየለች ቂንሶ ሚስትነቷን እንዲሁም ተጠሪዎች እና አመልካች ወራሽነታችንን አረጋግጠን በሻሸመኔ ከተማ አራዳ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ስፋቱ 420 ካ.ሜትር መሬት ላይ የተሰራ የማይንቀሳቀስ ንብረት እና በአባታችን ስም የሚታወቅ የንግድ ሱቅ ወርሰናል፡፡ እናታችን በሞት ከተለየችን በኋላ ተከራካሪ ወገኖች በሽማግሌዎች አማካኝነት በተደረገ ውል ንብረቶቹን በጋራ እያስተዳደርን ባለንበት አመልካች የሟች እናታችን ወራሾች መሆናችንን በመቃወም ኑዛዜ አለ ቢልም ኑዛዜው በሕግ መሰረት ግልጽ ኑዛዜ ማሟላት ያለበትን መስፈርት የሚያሟላ ባለመሆኑ እንዲሰረዝልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አመልካች ተከሳሽ በመሆን ለክሱ ባቀረቡት መልስ አከራካሪው ኑዛዜ በፍ/ቤት የተመዘገበ ስለሆነ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት እና ሌሎችን ምክንያቶችን በመጥቀስ ኑዛዜው ሕጋዊ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ሰምቶ ኑዛዜው ፍ/ቤት ቀርቦ የተመዘገበ ስለሆነ ስልጣን በሌለው አካል ዘንድ በመመዝገቡ ምክንያት ኑዛዜው ይሰረዛል የሚል ሕግ የለም በማለት የተጠሪዎችን ክስ ባለመቀበል በመዝገብ ቁጥር 16716 ላይ ወስኗል፡፡

የሰበር ተጠሪዎች የይግባኝ አቤቱታ ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ የተደረገው ኑዛዜ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ ማሟላት ያለበትን መስፈርት አላሟላም፡፡ በተጨማሪም ኑዛዜው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾችን ያለ ምክንያት ከውርስ የነቀለ ስለሆነ በሟች በ18/06/2008 ዓ/ም የተደረገው ኑዛዜ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ አንቀጽ 348(1) መሰረት በመሻር በመዝገብ ቁጥር 44192 በሆነው መዝገብ ላይ ወስኗል፡፡

የሰበር አመልካች የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም «የፍታብሔር ክርክር ጉዳይን በተመለከተ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ በሚኖሩ ነዋሪዎች መካከል ለሚነሱ የንብረት እና ይዞታ ክርክርን በተመለከተ የኦሮሚያ ወረዳ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የሥረ ነገር ስልጣን ያላቸው መሆን



ኑኪል ግልባጭ ... ኑባላት ፊርማ

አለመሆኑን» በተመለከተ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምርምርና ትብብር ዳይሬክቶሬት በኩል የሕግ ምርመር ተደርጎ እንዲቀርብ በማድረግ እና በውጤቱም ላይ የችሎቱ ዳኞች በፓናል ምክክር አድርገው ችሎቱ ከያዘው ጉዳይ በተጨማሪ ሌሎች ሰባት ተመሳሳይ የሆኑ መዝገቦችን በአንድነት መርምሮ የሚከተለው አቋም ላይ ደርሷል።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በፌዴራል እና በክልል የተዋቀረ መሆኑን፣ ይህም በሁለቱም ደረጃ ሶስቱም የመንግስት አካላት የተዋቀሩ መሆኑን፣ የፌዴራል እና የክልል መንግስት አካላት ስልጣን ደግሞ በሕገ መንግስቱ የተከፋፈለ መሆኑን እና እነዚህም አካላት አንዱ ለአንዱ የተሰጠውን ስልጣን ማክበር ያለባቸው ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50 ንኡስ አንቀፅ (1)፣ (2) እና (8) ሥር ተደንግጓል። የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች በሁለቱም የመንግስት አካላት ደረጃ የተቋቋሙ መሆናቸው ግልጽ ነው።

የሀገሪቷ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይ እና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ያለው ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ባለው የሕግ ስህተቶችን ማረም የሚችል ስልጣን አይቶ የሰበር ስልጣን ስለመሆኑ፣ በክልል ደረጃ ደግሞ በክልል ጉዳዮች ላይ የበላይ እና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሆን እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ የክልል ጉዳዮችን በተመለከተ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኙት ጉዳዮች የሕግ ስህተት ተፈጽሞባቸው ከተገኘ በሰበር ስልጣኑ አይቶ ማስተካከል የሚችል ስለመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(1፣2 እና 3) ሥር ተደንግጓል።

የፌዴራል ፍርድ ቤት ወይም የክልል ፍርድ ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው በማየት ውሣኔ ከመስጠታቸው በፊት ከመሰረቱ ጉዳዩ የፌዴራል መንግስት ስለመሆኑ ወይም የክልል ጉዳይ ስለመሆኑ መለየት አለበት። በሌላ በኩል በሕገ መንግስቱ ጉዳዩ " በፌዴራል መንግስት ስልጣን ሥር የሚወድቅ ጉዳይ ከሆነ የወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ተቀብሎ የማየት ስልጣን እንደሌለው እና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ደረጃ ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ስልጣን የሌለው ይሆናል፣ የሥረ ነገር ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሣኔ ደግሞ በይግባኝ ወይም በሰበር ታይቶ የሚሻር ስለመሆኑ በሥ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ አንቀጽ 9(2) ሥር ተደንግጓል፡

በሀገራችን በሕገ መንግስት ተዘርግቶ ባለው የፌዴራል ሥርዓት ውስጥ የፌዴራል እና የክልል መንግስት ስልጣን ክፍፍል የሚመራበት ከላይ በአጭሩ የተገለጸው ሲሆን፣ ለኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች ቀርበው በመታየት ላይ ከሚገኙት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ጉዳዩ የክልል መንግስት

ስልጣን ስለመሆኑ ወይም የፌዴራል መንግስት ጉዳይ ስለመሆኑ በመለየት ረገድ ሕገ መንግስቱ እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1)(ሸ) ጋር በአንድነት ሲታይ በኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች ዳኞች መካከል አከራካሪ መሆኑ በሚሰጠው ውሣኔዎች ውስጥ የተለያየ አቋም እንዲኖር አድርጓል። ይህ ደግሞ የውሣኔን ተገማችነትን እና ተመሳሳይነት የሚያሳጣ እና ባለ ጉዳዮችን ላልተገባ ወጪ የሚያጋልጥ በመሆኑ ባለ ጉዳይ እና ሕዝቡ በሕግ እና ፍርድ ቤት ላይ እምነት እንዲያጡ የሚያደርግ መሆኑ የሚታመን ነው።

በዚህ በኩል ለተፈጠረው ችግር የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1)(ሸ) ሥር የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን በተመለከተ በሁለቱ ክልሎች በቋሚነት በሚኖሩ ሰዎች መካከል ለሚነሳ ጉዳይ ወይም በአዲስ አበባ ከተማ እና በክልል ከተሞች ነዋሪዎች መካከል የሚነሱ ጉዳዮች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ነው በማለት ተደንግጓል። የዚህ አዋጅ ድንጋጌ ተከራካሪዎች የሚኖሩበት ቦታ ብቻ እንደ መስፈርት በመውሰድ ተከራካሪዎች የሚከራከሩበት ጉዳይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው። ከዚህም ጋር በተያያዘ በኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አከራካሪ የሆኑት እና በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መፍትሄ እንዲያገኝ ከተፈለገ የፌዴራል መንግስት እና የክልል መንግስት ፍርድ ቤቶችን የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን በመለየት ውስጥ የተፈጠረ የሕግ ትርጉም ልዩነት ነው።

ይኸውም 1ኛ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1፣ሸ) ላይ በግልጽ ስለተቀመጠ፣ ተከራካሪዎቹ የሁለት ክልል ነዋሪዎች ወይም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የኦሮሚያ ክልል ነዋሪ ከሆኑ ጉዳዩን ከግንዛቤ ማስገባት ሳያስፈልግ የፌዴራል ስልጣን ይሆናል፤ ጉዳዮች በዚህ አግባብ ካልታዩ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በአዋጁ በመጠቀም በክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች የሥረ ነገር ስልጣን ሳይኖራቸው ወሰኑ በማለት የሚሽር ስለሆነ፣ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.144613 ቅጽ 23ኛ ላይ ታትሞ በወጣው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት የሚያስገነዝብ ስለሆነ በአዋጁ መሰረት ሰራን የሚያሰኝ ነው።

ሁለተኛው ደግሞ በሀገራች በፌዴራል እና በክልል መንግስታት መካከል ስልጣን የሚከፋፈለው በሕገ መንግስቱ ስለሆነ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት ደግሞ ይህንን በጉዳዮች ከፋፍሎ ያስቀመጠ ስለሆነ፣ የበላይ እና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ በሕገ መንግስቱ ተደንግጎ ስላለ (የተከራካሪዎችን ቋሚ አድራሻ ብቻ መሰረት በማድረግ ጉዳዩ የክልል መንግስት

ወይም የክልል መንግስት አይደለም የሚባል ከሆነ ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ሕገ መንግስታዊ መብት ላይ በሥርዓቱ የተዘረጋውን መብት ችግር ውስጥ ሊያስገባ ስለሚችል አዋጁ ከሕገ መንግስቱ ጋር ታይቶ ሥራ ላይ መዋል አለበት።

በዚሁ መሰረት ተከራካሪዎች የሚከራከሩበት ጉዳይ የክልል ጉዳይ የሆኑ እንደ ቤተሰብ ጉዳይ፣ ውርስ፣ የመሬት አስተዳደር፣ በኦሮሚያ ክልል የተደረጉ ወይም የተፈጸሙ ውሎች ከሆነ ከተከራካሪዎች ውስጥ አንዱ የሌላ ክልል ነዋሪ ወይም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ከሆነ የክልል ጉዳይ ተብሎ ሊታይ ይገባል የሚል ነው።

ሦስተኛ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚመሩበት አዋጅ እንጂ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የሚመሩበት ሕግ ነው ተብሎ እንደ ሞዴል ተወስዶ ያልወጣ ስለሆነ የዚህ ዓይነት ጉዳይ ሲፈጠር ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለውን ለመለየት በሥራ ላይ ካለው ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ጋር በሚጣጣም በሥራ ላይ ማዋል መፍትሄ ነው በማለት የሚያነሱት ነው። ስለዚህ ይህ ችሎት ይህ ጉዳይ ወደ ፌዴሬሽን ሕግ ተርጓሚ ምክር ቤት ተልኮ መፍትሄ ማግኘት አለበት በሚል አቋም የሚከተለውን ትዕዛዝ ሰጥተናል።

**1ኛ)** የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 የሆነው የፍትሐ ብሔር የሥረ ነገር ስልጣንን በተመለከተ አንቀጽ 5(1)(ሸ) ሥር " የተከራካሪዎች ቋሚ የመኖሪያ ቦታ" ብቻ እንደ መስፈርት በመውሰድ፣ ተከራካሪዎች የሚከራከሩበት ጉዳይ በፌዴራል መንግስት ስልጣን ሥር ብቻ የሚወድቅ ጉዳይ ስለመሆኑ እና መፍትሄ የሚሰጥበት ሕግ በፌዴራል ሕግ ብቻ ስለመሆኑ ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ (ለምሳሌ በእጃችን ያለው የውርስ ንብረት እና ይዞታ መሬት ክርክርን፣ ወራሽነትን መቃወም ወይም ወራሽነት ይረጋገጥልኝ በኦሮሚያ ክልል በሚገኝ ይዞታ መሬት እና ንብረት እና የተወራሽ የመኖሪያ አድራሻም በሞተበት ጊዜ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚኖር፣ የአስተዳደር ወይም የገጠር መሬት አጠቃቀም ክርክር ወይም በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኝ የከተማ መሬት፣ በኦሮሚያ ክልል በሚገኝ ንብረት ወይም ይዞታ መሬት ላይ የተነሳ ሁከት ይቁም ክርክር፣ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚሰበሰብ እቁብ ወይም በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኝ ንብረት ባለቤትነት ክርክር ከግንዛቤ ውስጥ ሳያስገባ) የደነገገው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(2፣8)፣78(3) እና 52(1) ጋር ሲታይ ሕመንግስታዊ ነው ወይስ አይደለም? በሕገ መንግስት ለክልል መንግስቶች የተተው የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች እና የክልል መንግስታትም ጉዳዩን በተመለከተ ሕግ አውጥተው የሚያስተዳድሩበት የቤተሰብ

ሕግ፣ የመሬት ውርስ ፣ የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጥ እና ከመሳሰሉት ጋር ሲታይ ሕገ መንግስታዊ ነው ወይስ አይደለም?

**2ኛ)** በአዋጁ ድንጋጌ ተራ ቁጥር 1ኛ ሥር የተገለጸው ሕገ መንግስታዊ ነው የሚባል ከሆነ፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ውስጥ ክልል በመሆን ባልተቋቋመችበት እና መገኛ ቦታዋ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ውስጥ መሆኑ ተገልጾ ባለበት፣ ከምንም በላይ ደግሞ አዲስ አበባ ከተማ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ዋና ከተማ መሆኗ በተሻሻለው የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 94/2007 አንቀጽ 2(3) ሥር የተደነገገው በተጨባጭም በሥራ ላይ ውሎ ካለው ጋር ሲታይ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1)(ሸ) ስር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የኦሮሚያ ክልል ነዋሪዎች እንደ ተለያየ ክልል ነዋሪዎች በመውሰድ ከላይ የተገለጹት የፍትሐ ብሔር ክርክሮች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ጉዳዮች ማድረግ ሕገ መንግስታዊ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን በተመለከተ የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው መሆኑን ችሎቱ ስላመነበት ወደ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት ፌዴሬሽን ምክር ቤት መርቷል።

## ክፍል ሁለት

## የጉባኤው ጉዳዩን የማጣራት ሂደት

ጉባኤው የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበውን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ በመመርመር በጉዳዩ ላይ የባለሙያዎችን ምክር ሃሳብ መስማት አስፈላጊ በመሆኑ ሙያዊ ምክረ-ሐሳብ እንዲያቀርቡ የተለያዩ ተቋማትን ጋብዟል። ከተጋበዙት ተቋማት መካከል ምክረ ሃሳብ ያቀረቡት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር፤ የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ዐቃቢ ሕግ፤ የቤኒሻንጉል ብ/ክ/መንግስት ዓቃቤ ሕግ፤ የአማራ ብ/ክ/መንግስት ዓቃቤ ሕግ፤ የፌደራል የፍትሕ እና የሕግ ኢንስቲትዩት፤ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የህግና ፌደራሊዝም ኮሌጅ፤ ሐረማያ ዩኒቨርስቲ፤ የኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርስቲ፤ የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት የሕግ ማሰልጠኛና ምርምር ኢንስቲትዩት፤ የሕገ መንግሥት እና ፌደራሊዝም አስተምህሮ ማዕከልና የኢትዮጵ የፌደራል ጠበቆች ማህበር ናቸው።

ተቋማቱ በፅሁፍ እና በጉባኤው የመስማት ሂደት ላይ ያቀረቡአቸው ምክረ-ሐሳቦች ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል። ጉባኤው ከያዘው ጭብጥ አንፃር ምክር ሃሳቦቹን እንደ ግብአት ተጠቅሟል።

## ክፍል ሶስት

## የአብላጫ ድምጽ ውሳኔ

በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለጉባኤው የተላከው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ እና ከባለሙያዎች የቀረቡ የሙያ አስተያየቶች ይዘት ጉባኤው ከግምት በማስገባት ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት እንዲያመች የያዛቸው ጭብጦች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል መርህ ምንድነው?

2. መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች፣ በክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ፣ በክልል እና በድሬዳዋ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ጉዳዮች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን እንዲሆን መደንገጉ ሕገ መንግስታዊ ነው ወይ?

3. ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ከተያዙት ጭብጦች አንጻር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል 'ሸ' ሕገ መንግሥታዊ ነው አይደለም?

### 1. በሕገ መንግሥቱ የተደነገገውን የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል መርህ በተመለከተ፣

#### 1.1 የሕገ መንግስቱ ስልጣን ክፍፍል መርህ አጠቃላይ ገጽታ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 1 መሠረት ፌዴራላዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት አወቃቀር እንደሚከተል ደንግጓል፡፡ በዚህም አግባብ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግስትና በክልሎች የተዋቀረ እንደሆነ በአንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 1 ተመላክቷል፡፡ የፌዴራሉ መንግስትም በክልሎች የተዋቀረ እንደሆነ በአንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አዲስ አበባን በተመለከተ የፌዴራሉ መንግስት ርዕሰ ከተማ እንደሆነች እና የከተማው መስተዳድርም ለፌዴራል መንግሥቱ ተጠሪ እንደሚሆን በአንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ ከ1 እስከ 3 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ መንግሥት የሚያቋቁሙት በሕገ መንግሥቱ መሠረት የተዋቀሩት ክልሎች መሆናቸውንና አዲስ አበባን በተመለከተ ግን ተጠሪነቷ ለፌዴራሉ መንግስት እንደሚሆን ነው፡፡

ክልሎች የፌዴራሉን መንግስት ያቋቋሙ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራሉ መንግስት እና ክልሎች ያላቸው ስልጣን በሕገ መንግስቱ ክፍፍል ተደርጓል። በዚህ መሠረት የፌዴራሉ መንግስትና ክልሎች በተለምዶ የሚታወቁት ሦስት የመንግስት አካላት ማለትም ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት ስልጣን እንደሚኖራቸው በአንቀጽ 50(2) ተመላክቷል። ሕገ መንግስቱ የፌዴራልና የክልሎች ዋና ዋና ስልጣንና ተግባር በአንቀጽ 51 እና 52 እንደቅደም ተከተላቸው ዘርዝሯል። በዚህ ረገድ ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 51 የፌዴራሉ መንግስት ስልጣንና ተግባር በዋናነት ትኩረት የሚያደርገው አንድ የጋራ የኢኮኖሚና ፖለቲካ ማሕበረሰብ ከመፍጠር ጋር የተያያዙ፣ የአገሪቷን የውጪና የውስጥ ደህንነት ጉዳይ የሚመለከቱ፣ የአገሪቷን የውጭ ግንኙነትን የሚመለከቱ፣ ክልሎችን የሚያስተሳስሩ መሠረተ ልማቶችን የማልማትና የማስተዳደር የሚመለከቱ ወዘተ ጋር የተያያዙ ናቸው።

የክልሎች ስልጣንና ተግባርን በተመለከተ፣ ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 52(1) መሠረት ለፌዴራል መንግስት ወይም ለፌዴራሉ መንግስትና ለክልሎች በጋራ በግልጽ ያልተሰጠ ሥልጣን የክልል ሥልጣን እንደሚሆን ደንግጓል። ይህም የሚያሳየው ሕገ መንግስቱ የክልሎች ስልጣን አንድ በአንድ ከመዘርዘር ይልቅ ለፌዴራል መንግስት ወይም ለፌዴራልና ለክልሎች በጋራ የተሰጡ ስልጣኖች በተለይ በመዘርዘር ቀሪው በግልጽ ያልተሰጠ ስልጣን ለክልሎች መስጠት ነው። በመሆኑም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 52(2) የተዘረዘሩት የክልሎች ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሎች በሕገ መንግስቱ ለፌዴራል መንግስት ወይም ለክልሎችና ለፌዴራል መንግስት በጋራ በግልጽ ያልተሰጡ ስልጣንና ተግባራት አላቸው ማለት ነው።

ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 51 ለፌዴራል መንግስት የተሰጡ ስልጣንና ተግባራት መሠረት በማድረግ የሕግ አውጪው እና የአስፈጻሚው አካል አወቃቀርና ስልጣንና ተግባራት በምዕራፍ ስድስት ከአንቀጽ 53-68 እንዲሁም በምዕራፍ ስምንት ከአንቀጽ 72-77 እንደቅደም ተከተላቸው በዝርዝር ደንግጓል። ሕገ መንግስቱ በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች ስለ ሕግ አውጪው ስልጣንና ተግባር እንዲሁም የአስፈጻሚውን ስልጣንና ተግባር በተመለከተ ሲደነግግ ስለ ክልሎች ሕግ አውጪ እና አስፈጻሚ በተመለከተ የደነገገው ነገር የለም። በፌዴራሉ ሕግ አውጪ እና በክልሎች ሕግ አውጪዎች ወይምሕና በፌዴራሉ አስፈጻሚ እና በክልሎች አስፈጻሚዎች መካከል ሊኖር ስለሚችለው የስራ ግንኙነትም የደነገገው ነገር የለም። ይህም የሚያሳየው ሕገ መንግስቱ በፌዴራሉ እና በክልሎች ሕግ አውጪና አስፈጻሚ አካላት መካከል ግልጽ የስልጣን

ክፍፍል እንዲደረግ የሚፈልግ ሲሆን በፌዴራሉ እና በክልል ፍርድ ቤቶች መካከል ግን ግልጽ የስልጣን ክፍፍል አለማድረጉ ነው።

## 1.2. በፌዴራል እና ክልል ፍርድ ቤቶች መካከል በሕገ መንግስቱ ግልጽ የስልጣን ክፍፍል ያልተደረገ ስለመሆኑ

የፍርድ ቤቶችን አወቃቀርና ሥልጣን የሚመለከተው ምዕራፍ ዘጠኝ ከላይ በምዕራፍ ስድስትና ስምንት ከተመለከተው በተለየ አግባብ ፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን በዝርዝር ከመደንገግ ይልቅ የተከተለው አካሄድ ስልጣንና ተግባራቸውን በጥቅሉ መደንገግ ነው። በዚህም በአንቀጽ 80(1) መሠረት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት *"በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል"* በማለት ከደነገገ በኋላ በንዑስ አንቀጽ ሁለት የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት *"በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል። በተጨማሪም የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል"* በማለት ደንግጓል፡ የፌዴራል ሕገ መንግስቱ የፌዴራል እና የክልል የፍርድ ቤቶች ስልጣንን በተመለከተ በፌዴራል ጉዳይ እና በክልል ጉዳይ እንደቅደም ተከተላቸው ስልጣን እንደመኖራቸው ከመደንገግ ውጪ የፌዴራል ጉዳይ እና የክልል ጉዳይ ምንነት በዝርዝር አልደነገገም። ይህም የሚያሳየው የፌዴራል ጉዳይ እና የክልል ጉዳይ የሚለው አገላለጽ በዝርዝር የሚወሰነው ሕግ አውጪው በሚያወጣው ሕግ መሆኑ ነው። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ያወጣውም ይህንን በሕገ መንግስቱ የተገለጸው ድንጋጌ ወደ ትግበራ ለማስገባት ነው።

ከፌዴራል ሕገ መንግስቱ ለመረዳት የሚቻለው በፌዴራልና በክልል ሕግ አውጪና ሕግ አስፈጻሚ መካከል ፍጹም በሚባል አግባብ በስልጣን ክፍፍል ረገድ እንዲለያዩ የተደረገ ሲሆን የዳኝነት ስልጣንን በተመለከተ የክልል ፍርድ ቤቶች የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ደርበው እንዲሰሩ ሕገ መንግስታዊ ውክልና ከማግኘታቸው በተጨማሪ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ዝርዝሩ በሕግ በሚወሰነው አግባብ *"ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን"* ተሰጥቶታል። በዚህም የክልል ፍ/ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል የሚል አቤቱታ ሲቀርብለት ዝርዝሩ በሕግ በሚወሰነው አግባብ መርምሮ የመወሰን ስልጣን በአንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል 'ሀ' ተሰጥቶታል። ይህም የሚያሳየው ሕገ መንግስቱ በፌዴራል እና በክልል ፍርድ ቤቶች መካከል ጥብቅ የሆነ የስልጣን ክፍፍል ስርዓት እንዲኖር አለመፈለጉን ያሳያል።

የዳኞች አሿሿምን በተመለከተም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኞች ሹመት የሚከናወነው የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በእጩዎቹ ላይ ያለውን አስተያየት ከሰጠ በኋላ በክልሉ ምክር ቤት እንደሚሆን በአንቀጽ 81(4) ተደንግጓል። ይህ የሚያሳየው በሕገ መንግስቱ በፌዴራልና በክልል የዳኝነት ስልጣን መካከል ትስስር እንዲኖር ለማድረግ የተቀረጸ መሆኑ ነው። ይህን በሚያጠናክር አግባብ ሕገ መንግስቱ አንቀጽ 79 በፌዴራልና በክልል ደረጃ የሚሾሙ ዳኞች ያላቸው ነጻነት እና ተጠያቂነትን በተመለከተ የሚመሩበት መርህ ጭምር ተመሳሳይ እንደሆነ ተመላክቷል። ከዚህ የምንረዳው የዳኝነት አካሉ ስልጣንና ተግባር በሚመለከት ሕገ መንግስቱ በፌዴራል እና በክልል ሕገ መንግስት ለየብቻው ከመደንገግ ይልቅ በፌዴራሉ ሕገ መንግስት እንዲወሰን እንደፈለገ ነው።

## 1.3 የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች የሥረ ነገር ስልጣንን ስለመወሰን

የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች የሥረ ነገር ሥልጣን ለመወሰን መሠረት ሊሆን የሚችለው በአንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመላከተው የፌዴራል ጉዳይ እና የክልል ጉዳይ የሚለው አገላለጽ ነው። ሕገ መንግስቱ በዚህ ድንጋጌ በፌዴራል ጉዳይ እና በክልል ጉዳይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል በማለት የሚጠቅሳቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትን የተመለከተ ብቻ እንጂ የከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን በተመለከተ የደነገገው ነገር የለም። ከዚህ አንጻር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እና የክልል ፍርድ ቤቶች በምን ጉዳይ የሥረ ነገር ስልጣን እንደሚኖራቸው የተጠቀሰ ነገር የለም። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደቅደም ተከተላቸው በፌዴራል ጉዳዮች እና በክልል ጉዳዮች ስልጣን አላቸው የሚለው አገላለጽ ለበታች ፍርድ ቤቶችም እኩል ተፈጻሚነት ይኖረዋል ብንልም የፌዴራል ጉዳይ እና የክልል ጉዳይ ምንነት በሕግ ካልተወሰነ በቀር ሕገ መንግስቱ በቂ መልስ አይሰጥም።

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 51 እና 52 ለፌዴራል መንግስት እና ለክልል መስተዳደሮች በዝርዝር የተሰጡት ስልጣኖች የፌዴራልና የክልል ጉዳይን ለመለየት እንደ መነሻ እንጠቀምባቸው የሚባል ከሆነም አብዛኛው ስልጣን ለፌዴራሉ መንግስት የተሰጠ በመሆኑ የፍትሕ ተደራሽነት ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ የሚፈጥር ይሆናል። ለምሳሌ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና የሠራተኛን ሕግ በተመለከተ ሕግ የማውጣት ስልጣን እንደሚኖረውና በፌዴሬሽን ምክር ቤት አንድ የኢኮኖሚ ማሕበረሰብ ለመፍጠር ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የፍትሐ ብሔር ሕጎች የማውጣት ስልጣን እንደሚኖረው በአንቀጽ 55

ከንዑስ አንቀጽ 3 እስከ 5 ተደንግጓል። በዚህ አግባብ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ያወጣላቸው ጉዳዮች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ብቻ ሊታዩ ይገባል የሚባል ከሆነ በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከን የሚገኙ ዜጎች በአቅራቢያቸው ተደራሽ የሆነ ፍትሕ እንዳያገኙ በማድረግ በሕገ መንግስቱ ጥበቃ የተደረገለትን ፍትሕ የማግኘት መብትን ተግባራዊ ለማድረግ አይቻልም።

በፍርድ ቤቱ የተላከው የቤተሰብ፣ የገጠር መሬት እና የውርስ ክርክር የሚመለከቱ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ሕግ የማውጣት ስልጣንን በተመለከተም ሕገ መንግስቱ የክልል ምክር ቤቶች ይሆናል አይልም። ይልቁንም በአንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 2 የመሬትና የተፈጥሮ ሃብትን በተመለከተ ሕግ የማውጣት ስልጣን የፌዴራል መንግስት ከመሆኑ በተጨማሪ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት አንድ የኢኮኖሚ ማሕበረሰብ ለመፍጠር አይነተኛ ሚና ይጫወታሉ ተብለው የሚገመቱ የፍትሐ ብሔር ሕጎች የማውጣት ስልጣን በፌዴሬሽን ምክር ቤት አነሳሽነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊሰጥ የሚችልበት እድል አለ። ስለሆነም አሁን ባለው ሁኔታ የቤተሰብ ሕግ፣ የገጠር መሬትና የውርስ ሕግ የማውጣት ስልጣን ሙሉ በሙሉ ለክልል ምክር ቤቶች የተሰጠ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ አይቻልም። በአጠቃላይ ሕግ የማውጣት ስልጣንን ለፌዴራል መንግስት ወይም ለክልሎች መሰጠቱን መሠረት በማድረግ ጉዳዩ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉዳይ ወይም የክልል ፍርድ ቤቶች ጉዳይ ማድረጉ ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚጣጣም አይሆንም።

## 2 ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች መደበኛ ነዋሪዎች መካከል የሚኖር ክርክር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የማድረግ ሕገ መንግስታዊነትን በተመለከተ፣

### 2.1 ከሕገ መንግስቱ የፍርድ ቤቶች አወቃቀር ስርዓት አንጻር

ፌዴራሊዝምን የሚከተሉ አገሮች የዳኝነት አካል አወቃቀርን እና የስልጣን ክፍፍልን በተመለከተ የተለያየ አማራጮችን በተግባር ላይ ያውላሉ። በዚህም በፌዴራል እና በክልሎች መካከል ትይዩ የዳኝነት አካል በማዋቀር በሁለቱም መካከል የስልጣን ክፍፍል የሚደነግጉ ሕገ መንግስታት እንዳሉ ሁሉ የክልል ፍርድ ቤቶች ተጠሪነት ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲሆን በማድረግ አንድ ወጥ የዳኝነት ስርዓት የሚዘረጉ የፌዴራል ስርዓት የሚከተሉ አገሮችም አሉ። ስለሆነም አንድ አገር ትይዩ የዳኝነት ስርዓት በማዋቀሩ ወይም አንድ ወጥ ስርዓት መተግበሩ ፌዴራል ወይም አሃዳዊ ስርዓት ይከተላል ማለት አይደለም። የዳኝነት ስልጣንን በተመለከተ አንድ ወጥ የዳኝነት ስርዓት በአገሪቱ ደረጃ ያዋቀሩ ብዙ ቁጥር ያላቸው የፌዴራል ስርዓት

የሚከተሉ አገሮች በዓለም ላይ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ እና አውስትራሊያ ሕገ መንግስት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እና የክልል ፍርድ ቤቶች ራሳቸውን ችለው የተዋቀሩ ሲሆን በሕገ መንግስቱ የስልጣን ክፍፍል ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ሌሎች የፌዴራል ስርዓተ መንግስት የሚከተሉ አገሮች ለምሳሌ የጀርመን፣ ስዊዘርላንድ እና ሕንድ ሕገ መንግስት በምንመለከትበት ጊዜ በአገር አቀፍ ደረጃ አንድ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማቋቋም ክልሎች ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ የሆኑ ሌሎች ፍርድ ቤቶች እንዲያቋቁሙ እድል የሚሰጥ ነው፡፡

በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ትይዩ የሆኑ ፍርድ ቤቶች ያቋቋሙ አገሮች ለፌዴራልና ክልል ፍርድ ቤቶች በመርህ ደረጃ የስልጣን ክፍፍል የሚያደርጉት የሚያስፈጽሙትን ሕግ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በዚህም አግባብ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በፌዴራል ሕግ አውጪ የሚወጡ ሕጎች የማስፈጸም ስልጣን ያላቸው ሲሆን የክልል ፍርድ ቤቶች ደግሞ የክልል ሕግን የማስፈጸም ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያዩ ምክንያቶች የፌዴራል መንግስት ሕጎች በክልል ፍርድ ቤቶች እንዲፈጸሙ የፌዴራል መንግስት ውክልና የሚሰጥበት ዕድል ይኖራል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስትን በተመለከተ ከላይ በጭብጥ አንድ ላይ ለማየት እንደተቻለው በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ሶስት እርከን ያለው ትይዩ የፍርድ ቤቶች አወቃቀር ስርዓት የሚከተል ቢሆንም በፌዴራል እና በክልል ፍርድ ቤቶች ስልጣን መካከል ግንኙነት እንደሚኖር በሕገ መንግስቱ ተመላክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እንደ ሌሎቹ ትይዩ የፍርድ ቤቶች አወቃቀር ስርዓት የሚከተሉ አገሮች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወጡትን ሁሉንም ሕጎች እንዲያስፈጽም እና የክልል ፍርድ ቤቶችም በክልል ምክር ቤቶች የሚወጡ ሕጎችን እንዲያስፈጽሙ ተደርገው አልተቋቋሙም፡፡ ይልቁንም የክልል ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ በተሰጣቸው ውክልና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እስካልተነሳ ድረስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን ደርበው እንደሚሰሩ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉዳይ እና የክልል ፍርድ ቤቶች ጉዳይ በፌዴራል መንግስት ወይም በክልሎች ከሚወጡ ሕጎች ማስፈጸም ጋር ብቻ የተቆራኘ አይደለም፡፡

## 2.2. በአገር አቀፍ ደረጃ ውጤታማ የዳኝነት ስርዓት ከመገንባት አንጻር

በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ትይዩ ፍርድ ቤቶች ያቋቋሙ አገሮች ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች መደበኛ ነዋሪዎች በሆኑ ሰዎች መካከል ክርክር ሲኖር የዳኝነት ስልጣን ለፌዴራል ፍርድ

ቤቶች ይሰጣሉ፡፡ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን እንዲኖራቸው ያስፈለገበት ዋና ምክንያት በክልል ፍርድ ቤቶች ሊያጋጥም የሚችለውን አድልዎ ለመከላከል እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ በሌላ በኩል አሁን ባለንበት ዘመን ያለው የሰዎች እና የምርት እንቅስቃሴ፣ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መደበኛ ነዋሪዎች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚያጋጥሙ ክርክሮች እየበዙ ከምምጣታቸው ጋር ተያይዞ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት እንዲቻል ጉዳዩን የማየት ስልጣን ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች መስጠት የተሻለ አማራጭ እንደሚሆን የሚጠቁሙ ጥናቶች እየቀረቡ ነው፡፡ ለምሳሌ በአገር አቀፍ ደረጃ ባጋጠመ የፋብሪካ ምርት ብልሽት በተለያዩ ክልሎች በሚኖሩ ሰዎች ላይ ጉዳት ቢያደርስ ተከሳሹ በእያንዳንዱ ክልል በመሄድ ክርክር ከሚያደርግ ይልቅ ከሳሾች የሕብረት ክስ በፌዴራል ፍርድ ቤት ቢመሰርቱ ወጪ ቆጣቢ እና ተገማችነት ያለው ፍትሕ ለመስጠት ያስችላል፡፡

ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ነዋሪ በሆኑ ሰዎች የሚፈጠሩ ክርክሮች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን እንዲሆኑ የሚያስፈልገው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተደራሽነታቸው አገር አቀፍ የሆኑ ጉዳዮችን ለማጣራት የሚሰጡት ትእዛዝ አገር አቀፍ ተፈጻሚነት የሚኖረው ከመሆኑ ባሻገር ውሳኔ ከተሰጠ በኋላም ቢሆን ውሳኔውን ከአንድ ክልል በላይ መፈጸም የሚኖርበት ሲሆን ሁለቱም ተከራካሪዎች በሚኖሩበት ስፋራ የፌዴራል ፍ/ቤት የሚኖር በመሆኑ በፍ/ቤቱ የሚሰጠውን የአፈጻጸም ትእዛዝ በቀላሉ ለማስፈጸም ያስችላል፡፡ ስለሆነም ከሕገ መንግስቱ አላማ እና ከተግበራ ተስማሚነት አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ከአንድ ክልል በላይ የሚኖሩ ሰዎች መካከል ክርክር ሲኖር በፌዴራል ፍ/ቤቶች መታየቱ የተሻለ ውጤታማነት የሚያመጣ እና በፌዴራል መንግሥት እና በክልሎች መካከል መተሳሰር ለማምጣት የሚያስችለው ነው፡፡

### 2.3. ከሕገ መንግስቱ አጠቃላይ የስልጣን አወቃቀር አንጻር

ከሕገ መንግስቱ የስልጣን አወቃቀር አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም የፌዴራል መንግስት እና የክልሎች ስልጣን የተዘረዘረበት አንቀጽ 51 እና 52 መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በአንቀጽ 51 ለፌዴራል ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ስልጣኖች ስንመለከት ከአንድ ክልል በላይ የሚመለከቱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በአንቀጽ 51(9) ከሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን የሚያገናኙ አውራ መንገዶች፣ በአንቀጽ 51(12) በክልሎች መካከል የሚደረግ የንግድ ግንኙነትን፣ አንቀጽ 51(11) ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ ክልሎችን የሚያስተሳስሩ ድርበር ተሻጋሪ ወንዞችንና ሃይቆችን አጠቃቀም ወዘተ የተመለከቱ ጉዳዮች ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል መንግስቱ ነው፡፡

ሕገ መንግስቱ ከሁለት ክልሎች በላይ የሆኑ ጉዳዮች ለፌዴራል መንግስት የሚሰጥበት ምክንያት የፌዴራል መንግስት ክልሎችን የማስተሳሰርና የማስተባበር ሚና ስለሚጫወት ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ከአንድ ክልል በላይ ነዋሪ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚያጋጥሙ ክርክሮች እነዚህ ሰዎች የሚነሩባቸው ክልሎች ሁሉም የዳኝነት ስልጣን ስለሚኖራቸው በአንድ ጉዳይ የተለያዩ ውሳኔዎች እንዳይሰጡ ለመከላከል ሲባል የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ስልጣን ቢኖራቸው አንድ ወጥ የሆነ ውሳኔ ለማስጠት እና የፌዴራል መንግስት ክልሎችን የማስተባበርና የማስተሳሰር ሚናውን እንዲወጣ እድል የሚሰጥ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ከፌዴራል መንግስትና ከክልሎች ሕገ መንግስታዊ የስልጣን አወቃወር አንጻር ጉዳዩን ብንመለከተው አዋጁ ስልጣኑን ለፌዴራል ፍ/ቤቶች መስጠቱ ከሕገ መንግስቱ የተጣጣመ ያደርገዋል፡፡

የአዲስ አበባን እና የድሬዳዋን ጉዳይ በተመለከተ እንደቅደም ተከተላቸው በሕገ መንግስቱ እና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጣ ሕግ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ስልጣን የተሰጣቸው የከተማ መስተዳድሮች ናቸው፡፡ እነዚህ የከተማ መስተዳድሮች ተጠሪነታቸው ለፌዴራል መንግስቱ ነው፡፡ ስለሆነም በአንድ ክልል መደበኛ ነዋሪ የሆነ ሰው እና በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር ነዋሪ በሆነ ሰው መካከል የሚደረግ ክርክር በአንድ ክልል ውስጥ መደበኛ ነዋሪዎች በሆኑ ሰዎች መካከል ብቻ እንደሚደረግ ክርክር ሊቆጠር አይችልም፡፡ በእንደዚህ አይነት ክርክር ለፌዴራል መንግስቱ ተጠሪ በሆነ የከተማ መስተዳድር ነዋሪ እና በሌላ ክልል መደበኛ ነዋሪ መካከል የሚደረግ በመሆኑ ከላይ በጠቀስናቸው ምክንያቶች ክርክሩ በፌዴራል ፍርድ ቤት እንዲካሄድ ማድረግ የተሻለ ውጤት የሚያስገኝ በመሆኑ ይህ ሕገ መንግስታዊ ነው፡፡

## 2.4. ገለልተኛ እና ተገማች ፍትሕ ከማግኘት መብት አንጻር

በተለያዩ ክልሎች ነዋሪ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች የመዳኘት ስልጣን ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲሰጥ ከሚያስፈልግበት ምክንያቶች መካከል አንዱ አድልዎን ለማስቀረት እንደሆነ በዚህ ዙሪያ የተጻፉ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው በተለያዩ ክልሎች ነዋሪ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮች በክልል ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር እንዲሆን ማድረግ ዜጎች በፍትሕ ስርዓቱ ላይ እምኔታ እንዲያጡ እና ፍትሕ እንዲነፈጉ ምክንያት ሊሆን የሚችልበት እድል እንደሚኖር ነው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ የሕገ መንግስት ስርዓት እየገነባች የምትገኝ በመሆንዋ በክልሎች አዋሳኝ ቦታዎች እና በክልሎች መካከል ግጭቶች እና አለመግባባቶች የሚከሰቱበት ሁኔታ እንዳለ እሙን ነው። በአገር አቀፍ ደረጃ አንድ የጋራ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ማሕበረሰብ የመፍጠር አላማ በመያዝ እውን ለማድረግ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ የሚገኝ ሲሆን ከእነዚህ እንቅስቃሴዎች መካከል ዜጎች ከቦታ ቦታ ለስራ ሲንቀሳቀሱ የሚያጋጥማቸው ክርክር አድልዎ ይደረግብኛል ከሚል ስጋት ውጪ እንዲዳኙ ለማስቻል ስርዓት መፍጠር አንዱ ነው።

በመሠረቱ ፍርድ ቤቶች ነጻና ገለልተኛ ሆነው የተቋቋሙ ናቸው የሚል እሳቤ በጥቅሉ የሚወሰድ ቢሆንም እንደነ አሜሪካ እና አውስትራሊያ ባሉ ያደጉ አገሮችም ቢሆን በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ሰዎች መካከል የሚያጋጥም ክርክር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን እንዲሆን የተወሰነበት ምክንያት ፍርድ ቤቶች በሰዎች የሚመሩ ከመሆናቸው አንጻር ሊያጋጥም የሚችለውን ማንኛውንም የገለልተኝነት ችግር ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት እና የተከራካሪዎች በዚህ ረገድ የሚገጥማቸውን ስጋት ለመቅረፍ ነው። ስለሆነም በሁለት ክልሎች መካከል ነዋሪዎች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚያጋጥሙ ክርክሮች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን እንዲሆን ያስባሉ እሳቤዎች እና ምክንያቶች በተግባር በእኛ አገርም የሚስተዋሉ በመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁ. 1234/13 አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 1 ፊደል ሸ የመዳኘት ስልጣኑ ለፌዴራል ፍርድ ቤት መስጠቱ ዜጎች ከአድልዎ ስጋት ነጻ የሆነ ፍትሕ እንዲያገኙ የሚያስችል በመሆኑ ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚጣጣም ነው።

### 3. አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ሸ ሕገ መንግስታዊነትን በተመለከተ፣

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስትም በፌዴራል እና በክልል ፍርድ ቤቶች መካከል የተሳሰረ እና የተቆራኘ ግንኙነት እንዲኖራቸውና በዚህ አግባብ እንዲዋቀሩ ዓላማ በማድረግ የተደራጀ ነው። በዚህም የፌዴራል እና የክልል ዳኞች አሿሿም፣ የዳኞች ነጻነትና ተጠሪነት እንዲሁም በሁለቱም መካከል ያለው የዳኝነት ስልጣን ተመጋጋቢ እና ወጥ የሆነ የዳኝነት ስርዓት በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲኖር በሚያስችል አግባብ በሕገ መንግስቱ ተደንግጓል።

ከላይ በጭብጥ አንድ እና ሁለት እንደተመለከትነው መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች የሆኑ፣ በክልል እና በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ፣ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ የሆኑ ሰዎች የሚከሰት ክርክር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን እንዲሆን ያስፈለገበት ምክንያት ውጤታማ፣ ወጪ ቆጣቢ እና ተገማች የሆነ የፍትሕ ስርዓት ለመገንባት ነው። ይህንን ሃሳብ በሚያጠናክር

አግባብ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁ. 1234/13 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል 'ለ' የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የክልል፣ የአዲስ አበባ ወይም የድሬዳዋ ከተሞችን ሕግ የሚመለከት ሆኖ ሲገኝ የክልሉን ወይም የከተማውን ሕግ ተፈጻሚ እንደሚያደርጉ ተደንግጓል። ይህ የሚያሳየው የአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል 'ሸ' አላማ ውጤታማ ፍትሕ በአገር አቀፍ ደረጃ ለማስፈን በማሰብ እንጂ የክልሎች ወይም የከተማ አስተዳደሮቹ የዳኝነት ስልጣን ለመውሰድ ያለመ አይደለም።

ስለሆነም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2913 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል 'ሸ' የተደነገገው እና መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚፈጠር ክርክር የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን እንዲሆን ማድረጉ ከፌዴራል ሥርዓቱ አወቃቀር ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ሕገ መንግስቱን ጥሷል ሊባል አይችልም።

በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ጉባኤው በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል።

FDRE Council of Constitutional Inquiry

## ክፍል አራት

## የልዩነት ሃሳብ

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር 4ኛ፣ 6ኛ፣ 7ኛ እና 10ኛ ላይ የተጠቀሰው የጉባኤው አባላት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የልዩነት እና የማስማሚያ ሃሳብ እንደሚከተለው አቅርበናል። የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበውን የትርጉም ጥያቄ እና የቀረቡ የሙያ አስተያቶችን መሰረት በማድረግ የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ የሚከተሉት ጭብጦች ተይዟል።

1. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል መርህ ምንድነው?

2. መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች፣ በክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ፣ በክልል እና በድሬዳዋ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ጉዳዮች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን እንዲሆን መደንገጉ ሕገ መንግስታዊ ነው ወይ?

3. ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ከተያዙት ጭብጦች አንጻር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል 'ሸ' ሕገ መንግሥታዊ ነው አይደለም?

### 1. በሕገ መንግሥቱ የተደነገገውን የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል መርህን በተመለከተ፣

### 1.1የሕገ መንግስቱ ስልጣን ክፍፍል መርህ አጠቃላይ ገጽታ

የሀገራችን የኢትዮጵያ መንግሥት ስያሜ ፌዴራላዊና ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ሲሆን፣ የፌዴራሉ መንግሥትም በክልሎች የተዋቀረ መሆኑን ከሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 1 እና 46 (1) መረዳት ይቻላል። በኢትዮጵያ የተዋቀረው የፌዴራል ስርዓት የትይዩ (የመንታ) የፌዴራል (Dual federalism) የመንግሥት ስርዓት ነው። አንድ የፌዴራል ስርዓት የትይዩ (የመንታ) የመንግስት ስርዓት ስለመሆኑ ከሚረጋገጥበት መንገድ አንዱ የፌዴራል እና የክልል የሕግ አውጪ፣ የሕግ አስፈፃሚ እና የዳኝነት አካላት እንዲደራጁ ሲያደርግ ነው። በዚሁ መሰረት

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት የፌዴራል መንግሥትና ክልሉች የሕግ አውጪ፣ የሕግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካላት ያላቸው ስለመሆኑ የሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 50 ንኡስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት መሰረት ክልሎቹ እና የፌደራል መንግስቱ የህግ አወጪዎች፣ ህግ አስፈጻሚዎችና የዳኝነት አካላት (ፍርድ ቤቶች) በየዘርፋቸው በሕገ መንግስቱ በተሰጣቸው የስልጣን ገደብ ውስጥ ሙሉ ስልጣን ይኖራቸዋል። ሁለቱም የመንግስት አርከኖች የሌላውን ስልጣን የማክበርም ግዴታ አለባቸው።

ሕገ መንግስቱ በምዕራፍ አምስት ስር የስልጣን አወቃቀርና ክፍፍል ከአንቀጽ 50 እስከ አንቀፅ 52 እና የፌዴራል መንግስት ምክር ቤቶች ስልጣንና ተግባራት እንዲሁም የአስፈጻሚው አካል አወቃቀርና ስልጣንና ተግባራት በምዕራፍ ስድስት ከአንቀጽ 53-68 እንዲሁም በምዕራፍ ስምንት ከአንቀጽ 72-77 እንደቅደም ተከተላቸው በዝርዝር ደንግጓል።

አንድ የመንግስት ሥርዓት የፌዴራል የመንግስት ስርዓት የሚከተል መሆን አለመሆኑ አንዱና ዋነኛው መለያው እና መለኪያው በፌዴራል መንግስትና በክልል መንግስታት መካከል በሕገ መንግስት የተደነገገ የስልጣን ክፍፍል መኖሩ ነው። በፌዴራል መንግስትና በክልል መንግስታት መካከል የሕግ አውጪው የስልጣን ክፍፍል ካልተደረገ የመንግስት ስርዓቱ የፌዴራል የመንግስት ስርዓት መሆኑ ቀርቶ የተማከለ የመንግስት ስርዓት ይሆናል።

በፌዴራል መንግስትና በክልሉች መካከል የሚደረገው የስልጣን ክፍፍል በአይነትና በመጠን ሊለያይ ይችላል። በዓለም ላይ ያሉ የፌዴራል የመንግስት ሥርዓት የሚከተሉ ሃገራት በአብዛኛው የፌዴራል እና የክልል መንግስታት የስልጣን ክፍፍል በሶስት መልኩ ይደነግጋሉ። የመጀመሪያው ከፌዴራልና ከክልል መንግስታት የአንዱን ስልጣን በመዘርዘር የአንደኛውን የመንግስት ስልጣን ባለመዘርዘር የስልጣን ክፍፍል በሕገ መንግስት ይደነግጋሉ። ይህ የስልጣን ክፍፍል መርህ በጣም ቀላሉና በአሁን ጊዜ በተለያዩ የፌዴራል ሃገራት የሚተገበር ነው። ለምሳሌ አሜሪካ፣ ሲውዘርላንድና አስትሪያ በዚህ መልኩ የፌዴራል መንግስቱን ስልጣን በመዘርዘር የክልል መንግስትን ስልጣን ባለመዘርዘር በሕገ መንግስት ደንግገዋል። በተቃራኒው ካናዳ እና ህንድ ደግሞ የክልል መንግስት ስልጣን በመዘርዘር የፌዴራሉን መንግስት ሳይዘረዝሩ የስልጣን ክፍፍል አድርገዋል። ሁለተኛው የስልጣን ክፍፍል መርህ የሁለቱንም ማለትም የፌዴራልና የክልል መንግስታት ስልጣን እኩል በግልፅ መዘርዘር ነው። በዚህ መርህ መሰረት ሁለት የስልጣን ዝርዝር በሕገ መንግስት ተደንግጎ ይገኛል ማለት ነው። ሶስተኛውና

የመጨረሻው ደግሞ የሁለቱም መንግስታት ስልጣን ከተዘረዘረ በኃላ የሁለቱ መንግስታት የጋራ ስልጣን በተጨማሪ በጋራ የሚዘረዘርበት ሂደት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕገ መንግስትም ከላይ ከተመለከትነው የሃገራት ልምድ አንፃር የአሜሪካውን ሕገ መንግስታዊ የስልጣን ክፍፍል አይነት በመከተል የፌዴራል መንግስት ስልጣን በመዘርዘር ያልተዘረዘሩትን ስልጣኖች ደግሞ ለክልልች በመተው የስልጣን ክፍፍል ስለማድረጉ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 52 መረዳት ይቻላል፡፡

የሕገ መንግስቱ ምዕራፍ አምስትና ስድስት የፌዴራልና የክልል መንግስታት የስልጣን ክፍፍል ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራልና የክልል ሕግ አውጪ አካላት ስልጣን ክፍፍል ይደነግጋል፡፡ ሕገ መንግስቱ የፌዴራልና የክልሎች ሥልጣን በአንቀጽ 51 እና 52 እንደቅደም ተከተላቸው ዘርዝሯል፡፡ በአንቀፅ 51 ስር ለፌዴራል መንግስት በ21 ጉዳዮች ላይ የፌዴራል መንግስት የሕግ አውጪ ስልጣን እንዳለው ዘርዝሯል፡፡ የክልሎች ስልጣንና ተግባርን ደግሞ በሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 52(1) መሠረት ለፌዴራል መንግስት ወይም ለፌዴራሉ መንግስትና ለክልሎች በጋራ በግልጽ ያልተሰጠ ሥልጣኖች የክልል ሥልጣን እንደሚሆን ደንግጓል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ሕገ መንግስቱ የፌዴራል የሕግ አውጪ እና የክልል የሕግ አውጪ ስልጣን በተገቢው ሁኔታ የስልጣን ክፍፍል ያደረገ ስለመሆኑ ነው፡፡ የፌዴራሉ መንግስት የሕግ አውጪ አካል ስልጣን በመዘርዘርና የክልል የሕግ አውጪ አካል ስልጣን ደግሞ ያልተዘረዘሩት ስልጣኖች በመስጠት ክፍፍል አድርጓል፡፡

ከዚህ ከሕግ አውጪው ስልጣን ክፍፍል አንፃር የአብላጫው ድምፅ በሕገ መንግስቱ በምዕራፍ ስድስትና በምዕራፍ ስምንት የተደነገገው የፌዴራል መንግስት የሕግ አውጪ እና የሕግ አስፈፃሚ ስልጣን ብቻ እንጂ የክልሎችን የሕግ አውጪና የሕግ አስፈፃሚ ስልጣን በሕገ መንግስቱ አልደነገገም በማለት የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄውን ውድቅ ለማድረግ ትንታኔ መስጠቱን የማንቀበለው ነው፡፡ ሕገ መንግስቱ የፌዴራልና የክልል ሕግ አውጪ አካላት ስልጣን በዚህ መልኩ ከደነገገ የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል መርሁን ቀጥለን እንመለከት፡፡

**1.2 የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ስልጣን በሕገ መንግስቱ በግልጽ ክፍፍል ያልተደረገ በመሆኑ የፌዴራልና የክልል የሕግ አውጪ ስልጣን ክፍፍልን የሚከተል ስለመሆኑ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ውስጥ የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ክፍፍልን በተወሰነ መልኩ የምናገኘው በህገ መንግስቱ ምዕራፍ 9 ስር ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 78 መሠረት ሁለት ራሳቸውን የቻሉ መደበኛ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እና

የክልል ፍርድ ቤቶች እንደሚቋቋሙ ተደንግጓል። በርግጥ ሕገ መንግስቱ የክልል ፍርድ ቤቶች አወቃቀር ጭምር የደነገገ ሲሆን የፌዴራል ፍርድ ቤትን ግን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ብቻ በማቋቋም ሌላው በሕግ አውጪ አካል እንደሚቋቋም የሚፈቅድ ነው።

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ስር እንደተደነገገው የፌደራል ፍርድ ቤቶች በ"ፌደራል ጉዳዮች" ላይ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የሚኖራቸው ሲሆን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በነዚህ ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት አካል ነው። በተመሳሳይም የክልል ፍርድ ቤቶች በ"ክልል ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ስልጣን ይኖራቸዋል፣ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በክልል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት አካል ነው። ከእነዚህ የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች በፌዴራል እና በክልል ጉዳዮች ላይ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ እንጂ እነዚህ የፌዴራል እና የክልል ጉዳዮች ምን ምን ጉዳዮች እንደሆኑ ሕገ መንግስቱ በዝርዝር አይደነግግም።

በአብዛኛው የፌዴራል ስርዓት በሚከተሉ ሃገራት የፌዴራል እና የክልል መንግስታት የስልጣን ክፍፍል በዋነኛነት የሚደረገው የሕግ አውጪውን የስልጣን ክፍፍል ተከትሎ ነው። በሌሎች የፌዴራል መንግስታት ደግሞ የስልጣን ክፍፍሉ በሕግ አውጪው ላይ ተገድቦ የሚቆም ሳይሆን የፌዴራልና የክልል የሕግ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንም ጭምር በሕገ መንግስት ይከፋፈላል። በሌሎች ደግሞ ከሕግ አውጪውና ከሕግ አስፈፃሚው አካላት በተጨማሪ የዳኝነት አካላት ወይም የፍርድ ቤቶችም የስልጣን ክፍፍል በሕገ መንግስት ይደረጋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጥያቄ ሕገ መንግስቱ የፌዴራልና የክልል የሕግ አውጪ ስልጣን ብቻ በሚደነግግበት ጊዜ የሕግ አስፈፃሚውና የፍርድ ቤቶች የስልጣን ክፍፍል እንዴት ይሆናል የሚለው ነው።

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት የሌሎች ሃጋራትን ልምድ ማየት ተገቢ ነው። በፌዴራልና በክልል ፍርድ ቤቶች መካከል ግልፅና ዝርዝር የዳኝነት (የፍርድ ቤቶች) የስልጣን ክፍፍል ባልተደረገ ጊዜ ወይም ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ በማይኖር ጊዜ በተለይም ትይይዩ (የመንታ) የፌዴራል ስርዓት በሚከተሉ ሃገራት ያለው ልምድ የሚያስያው የዳኝነት (የፍርድ ቤቶች) ስልጣን የሚመነጨው ከህግ አውጪው ስልጣን ነው። ማለትም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በህገ መንግስቱ ለፌዴራል የህግ አውጪ አካላት የተሰጠውን ስልጣን ተከትለው በፌዴራል የህግ አውጪ አካል የወጡትን ህጎች የሚዳኙ ሲሆን የክልል ፍርድ ቤቶችም ለክልል ህግ አውጪ አካል በተሰጠው ጉዳይ ላይ ብቻ የዳኝነት ስልጣን የሚኖራቸው ይሆናል።

ለፌደራል ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን ወይም የፌደራል ጉዳዮች የሚባሉት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 51 እና 55 መሠረት የፌደራል መንግስቱ ስልጣንና ተግባር የሆኑና የፌደራል መንግስት በሚያወጣቸው ህጎች የሚገዙ ጉዳዮች ናቸው። በተመሳሳይም ለክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን ወይም የክልል ጉዳዮች የሚባሉት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 52 መሠረት በግልጽ የክልል መንግስታት ስልጣንና ተግባር የሆኑ እና ለፌደራል መንግስት በግልጽ በብቸኝነት ወይም በጋራ ያልተሰጡ ስልጣንና ተግባራት እንዲሁም የክልል መንግስታት በሚያወጡአቸው ህጎች የሚገዙ ጉዳዮች ናቸው

ለማሳያነትም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀፅ 55 ንኡስ አንቀፅ አንድ፤ ሁለት፤ ሶስት፤ አራትና ተከታዮቹ ስር የንግድ ህግን፤ የሰራተኛ ህግ እና የወንጀል ህግ የማውጣት ስልጣን የፌዴራሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስልጣን ስለመሆኑ ተደንግጓል።

ሌሎች በግልፅ ያልተደነገጉ የፍታብሄር ጉዳዮችን በተመለከተ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር ሲባል በፌዴራል መንግስት ህግ እንዲወጣላቸው የሚያስገድዱ ለመሆናቸው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ያመነባቸው ካልሆኑ በስተቀር በፍታብሄር ጉዳዮች ላይ ህግ የማውጣት ስልጣን የክልሎች እንደሆነ ተደንግጓል።

በተጨማሪም የከተማ እና የገጠር መሬትን በተመለከተ ደግሞ በአንቀፅ 55 ንኡስ አንቀፅ አንድ ስር መሬትና የተፈጥሮ ሃብትን በሚመለከት ህግ የማውጣት ስልጣን የፌዴራል መንግስት ሲሆን ህጉን የማስፈጸም ስልጣን ደግሞ የክልሎች እንደሆነ ተደንግጓል። በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት የገጠር መሬትን በሚመለከት ሕግ የማውጣት ስልጣን ለፌዴራል መንግስት ተሰጥቶ መሬት የማስተዳደር ስልጣን ደግሞ ለክልሎች የተሰጠ ነው።

የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ሕገ መንግስታዊ የዳኝነት ስልጣንን ከፍፍል መርሁ ከላይ የቀረበውና የሕግ አውጪውን የስልጣን ክፍፍል የሚከተል ስለመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 ሲረቀቅ በረቂቁ ላይ ከተደረገው ውይይትም መረዳት ይቻላል።

በዚህ ረቂት ህግ ውይይት ላይ የአዋጅ 25/88 ምንጭ ምንድነው ለሚለው ጥያቄ ፍትህ ሚኒስቴር በሰጠው አስተያየት የህጉ ምንጭ ሕገ መንግስቱና አዋጅ ቁጥር 40/85 መሆኑን በመጥቀስ የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን በተመለከተ ይህን ሃሳብ አቅርቧል፤-

> "የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች የስልጣን ክፍፍል መሠረት ሊሆን የሚገባው የፌዴራል ህጎችና የክልል ህጎች ሲሆን ነገር ግን የፌዴራል ህጎች ስለሌሉና የክልል

ህጎችም ገና ያልተጠናከሩበት ሁኔታ በመሆኑ የቀረበው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክፍፍል ሲታይ ግልፅ ያልሆኑ የሚመስሉ ነገሮች ስለመኖራቸው፤ በአዋጁ የቀረበውን ጉዳይ ለማስተናገድ መሰረት የሆነው በህገ መንግስቱ የተጠቀሱት የፌዴራል ፍርድ ቤት ሥልጣንና የፌዴራል ህጎች እንዲሁም ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ የሚነሱ ክርክሮችን ያያል በማለት እንደሆነ ጠቁመዋል"።

በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተደረገው ውይይት መረዳት የሚቻለው የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል መርሁ ከላይ እንደተጠቀሰው የፌዴራል እና የክልል ህግ አውጪ አካል ስልጣን (የፌዴራል እና የክልል) ህጎችን መሰረት ያደረገ እንደሆነ ነው።

በረቂቅ አዋጁ ላይ የተደረገው ውይይት መሰረት የፌዴራል እና የክልል የዳኝነት ስልጣን በሕገ መንግስቱ የፌዴራል እና የክልል ህግን መሰረት ማድረግ እንዳለበት ቢታመንም ስልጣኑን በአዋጅ መደንገግ ያስፈለገው የፌዴራልና የክልል ህጎች በሰዓቱ ባለመውጣታቸው ነው። ይህ በአርቃቂው እንደ ጊዜያዊ አማራጭ የተወሰደ እንጂ የሕገ መንግስቱ የፍርድ ቤቶች የስልጣን ክፍፍል መርህ በአዋጁ እንደተነገገው በመሆኑ አይደለም። ስለሆነም የአዋጁ ረቂቅ ውይይትም በተመሳሳይ የሚያጠናክረው የፌዴራል እና የክልል የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል መርህ የፌዴራል እና የክልል ህግ አውጪ አካል ስልጣንን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ ነው።

የፌዴራል እና የክልል የዳኝነት ስልጣን በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ በሕግ አውጪው እንዲወሰን መፍቀድ ሕግ አውጪው በፈለገው ጊዜ የፌዴራል የዳኝነት ስልጣኑን ሊያሰፋው ወይም እንዲያጠበው መፍቃድ ነው። ከላይ በሰፊው እንደተብራራው የፌዴራል እና የክልል የዳኝነት ስልጣን በመሰረቱ መዘርዘር ያለበት በሕገ መንግስትና በሕገ መንግስት ብቻ ነው። ሕገ መንግስቱ የስልጣን ክፍፍሉን በበቂ ሁኔታ ባልዘረዘረ ጊዜ ደግሞ የሁለቱን የስልጣን መጠንና ስፋት መወሰን ያለበት የሕገ መንግስት ተርጓሚ አካል እንጂ በፌዴራል ሕግ አውጪ አካል አይደለም። ለምሳሌ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ 25/88 በሁለት ክልል ነዋሪዎች መካከል የሚነሳ የፍትሐብሄር ክርክር የማየት ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንደሆነ ይደነግጋል። በአዲሱ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ደግሞ የፌዴራል የሕግ አውጪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን በማስፋት በሁለት ክልል ነዋሪዎች፤ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ ነዋሪዎች መካከል የሚነሳ የፍትሐብሄር ክርክር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ይሆናል በማለት ደንግጓል። ይህ ድንጋጌ ከቀድሞ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ በተወሰነ መልኩ የሰፋ ስልጣን ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች መስጠቱን ያመለክታል። እንዲህ

አይነት የፌዴራል እና የክልል የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል የፌዴራል የሕግ አውጪ አካል እንዲያወጣ መፍቃድ የክልሎችን ስልጣን መጋፋት ነው።

ስለሆነም በፍርድ ቤቱ የተላከው የቤተሰብ፣ የገጠር መሬት እና የውርስ ክርክር የሚመለከቱ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ ሕግ የማውጣት ስልጣንን በግልፅ ለፌዴራሉ መንግስት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 51 እና 55 እንዲሁም ሌሎች ድንጋጌዎች ያልተሰጠ ስልጣን ነው። በሕገ መንግስቱ በግልፅ ለፌዴራል መንግስት ያልተሰጠ ስልጣን ደግሞ የክልል መንግስታት ስልጣን እንደሚሆን ከሕገ መንግስቱ አንፅ 52 (2) መረዳት ይቻላል።

ከዚህ አንፃር የአብላጫው ድምፅ አሁን ባለው ሁኔታ በፍርድ ቤቱ የተላከው የቤተሰብ ሕግ፣ የገጠር መሬትና የውርስ ሕግ የማውጣት ስልጣን ሙሉ በሙሉ ለክልል ምክር ቤቶች የተሰጠ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ አይቻልም። በመሆኑም ሕግ የማውጣት ስልጣንን ለፌዴራል መንግስት ወይም ለክልሎች መስጠቱን መሠረት በማድረግ ጉዳዩ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉዳይ ወይም የክልል ፍርድ ቤቶች ጉዳይ ማድረጉ ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚጣጣም አይሆንም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ እና ትንታኔ በሕገ መንግስቱ በግልፅ ለክልል መንግስታት የተሰጠው ስልጣን የሚጥስ ነው። ስለሆነም ከላይ የተጠቀሰውን ምክንያት መሰረት በማድረግ የፌዴራልና የክልል የዳኝነት ስልጣን መርህ የፌዴራል እና የክልል የሕግ አውጪ ስልጣን የሚከተል (መሰረት) ያደረገ ነው።

2. **ጭብጥ ሁለት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2913 አንቀፅ 5 (1) (ሸ) የተደነገገው እና መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልል ነዋሪ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ጉዳዮች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን እንዲሆን መደንገጉ ሕገ መንግስታዊ ነው ወይ የሚል ነው።**

ከላይ እንደተገለፀው የፌዴራል እና የክልሎች የዳኝነት ስልጣን በግልፅ እና በዝርዝር በሕገ መንግስቱ ባለመደንገጉ ሃገራችን ከምትከተለው የፌዴራል የመንግስት ስርዓት አንፃር በሕገ መንግስት ትርጉም ከላይ የተቀመጠው መደምደሚያ ላይ መድረስ ይቻላል። በዚህ መደምደሚያ መሰረት የፌዴራል እና የክልል የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል የፌዴራል እና የክልል ህግ አውጪ ስልጣንን የሚከተል ነው። ቀጥሎ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው ጥያቄ ከዚህ መደምደሚያ አንፃር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5 ንኡስ አንቀፅ 1 (ሸ) ሕገ መንግስታዊነት መመርምር ተገቢ ነው።

FDRE Council of Constitutional Inquiry

በሕገ መንግስቱ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን እንዲያቋቁም ስልጣን የተሰጠው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው። ምክር ቤቱ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ሲያቋቁምና ሲያደራጅ የፍርድ ቤቶቹን የዳኝነት ሥልጣን በህግ የመዘርዘር ሥልጣን አለው። በተመሳሳይ የክልል ፍርድ ቤቶችም የየራሳቸውን የዳኝነት ፍርድ ቤቶች ሲያደራጁ የክልሉን የዳኝነት ሥልጣንም የክልል ምክር ቤቶች በህግ የመዘርዘር ሥልጣን አላቸው። የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሊያስናሳ የሚችለው አንዱ ጉዳይ የፌዴራል መንግስት የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የሥረ ነገር ሥልጣን ሲዘረዝር በሕገ መንግስቱ ለክልል ፍርድ ቤቶች የተተወውን ሥልጣን በመተላለፍ ሕግ ሲያወጣ ወይም የክልል የፍርድ ቤቶች የሥረ ነገር ሥልጣን የሚዘረዝር የክልል ሕግ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥረ ነገር ሥልጣን ስር በሚወድቁ ጉዳዮች ላይ ሕግ ሲያወጣ ነው።

አሁን ለትርጉም የቀረበው ጉዳይም ከዚሁ አንፃር የሚታይ ነው። የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በአንቀጽ 5 ንኡስ አንቀፅ 1 (ሸ) ስር የተደነገገው የብዛሃነት የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል መርህ ከላይ ከተመለከተውና በኢፌዲሪ ህገ መንግስት ውስጥ ከሰፈረው የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል መርሆች የተለየ ነው። ይህ ድንጋጌ የተከተለው የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል መርህ ምንጭ እና ምክንያት በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ከኢትዮጵያ የፌደራላዊ ስርዓት ጋር ተቀራራቢ የሆኑ የፌደራል ስርዓቶችን መመርምር እንዲሁም የፌዴራል ፍርድ ቤት አዋጅ ሲወጣ የተነሱትን ሃሳቦች ማየት አስፈላጊ ነው።

ይህ መርህ (diversity jurisdiction) ዳይቨርሲቲ ጁሪስዲክሽን ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን በአሜሪካ የፌደራል ህገ መንግስት አንቀጽ III (2-1) ስር ተደንግጎ ይገኛል። በተመሳሳይ በአውስትራሊያ ሕገ መንግስት አንቀፅ 75 ተመሳሳይ መርህ ተደንግጎ ይገኛል። ይህ በአሜሪካ የፌዴራል እና የክልል የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል ውስጥ የሚገኘው የብዛሃነት የዳኝነት ሥልጣን መርህ እንደሚገልጸው ክርክሩን ያስነሳው ጉዳይ በግዛቶች/ በክልሎች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ቢሆንም ተከራካሪዎቹ የተለያዩ ግዛት ነዋሪዎች/ ዜጎች ከሆኑ ከሳሹ ጉዳዩን ለፌዴራል ፍርድ ቤት ሊያቀርበውና የፌደራል ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ለማየት ይችላል በማለት ይደነግጋል። ይህ መብት ለከሳሹ ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ክስ የቀረበበት ተከሳሽም ክሱ በክልል ፍርድ ቤት ሲቀርብበት ጉዳዩ ወደ ፌዴራል ፍርድ ቤት እንዲዛወርለት ለመጠየቅ ይችላል። የዚህ ህግ ዋና አላማም በመሰረታዊነት አንድና አንድ ነው። እርሱም የክልል ፍርድ ቤቶች የክልላቸው ነዋሪ/ ዜጋ ላልሆነ ተከራካሪ ወገን ገለልተኛ የሆነ ፍትህ ላይሰጡ ይችላሉ የሚል ነው።

በአሜሪካ የፌዴራል ሥርዓት የክልል ፍርድ ቤቶች የክልላቸው ነዋሪ/ ዜጋ ላልሆነ ተከራካሪ ገለልተኛ የሆነ ፍትህ ላይሰጡ ይችላሉ የሚለው ሂሳቤ እና ዓላማ ከሃገሪቱ የመንግስት አመሰራረት እና የፌዴራል ሥርዓት አመጣጥ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የአሜሪካ ሃገር ወይም የሃገረ መንግስቱ የፌዴራል ሥርአት የተመሰረተው ቀድሞ በሌላ ሃገር ስር በነበሩ የተለያዩ ግዛቶች ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አዲስ ሃገር ለመመስረት አንድ ላይ የመጡት እነዚህ የተለያዩ ግዛቶች ጠንካራ አንድነት ያለው አዲስ ሃገር እና የፌዴራል ሥርዓት መመስረት የህልውናቸው መሰረት ነበር፡፡ ይህን ህልውናቸውን ለማረጋገጥ የሃገሪቱን አንድነት ሊያጠናክሩ የሚችሉ ማናቸውንም መርሆዎች መተግበር ግዴታ ነው፡፡ ከፍርድ ቤቶች የዳኝነት የስልጣን ክፍፍል መርህ አንፃርም በሁለት ክልል ነዋሪዎች መካከል የሚነሳ ክርክር የፌዴራሉ መንግስት ፍርድ ቤት እንዲያይ ሥልጣን የተሰጠው ለዚሁ ነው፡፡

ይህንኑ መሰረት በማድረግ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2014 አንቀፅ 5 ንኡስ አንቀፅ 1 ሸ የተደነገገው የብዝሃነት መርህ መነሻው ወይም ምንጩ ምንድነው የሚለውን ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

አንዳንድ ፀሃፍት የዚህ ምንጭ የአሜሪካው እና የሌሎች መሰል የፌዴራል ሃገራት የተወሰደ ልምድ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ የብዝሃነት የዳኝነት ስልጣን መርህ የተወሰደው ከአሜሪካ ቢሆን ዓላማው ግን እንደ አሜሪካው ልምድ በክልሎች መካከል ሊኖር የሚችለውን አድሎ ለመከላከል ብቻ አይደለም ይላሉ፡፡ ለምሳሌ ፍትህ ሚኒስቴር በሰጠው አስተያየት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 የተከራካሪ ወገኖችን ነዋሪነት ቦታ መሰረት ማድረጉ አላማው ፍትሃዊነትና የፌዴራል መንግስቱን ግብ ከሚሟላት አንፃር በራሱ የክልሎችን ስልጣን የሚጋፋ ካለመሆኑም በላይ የክልል መሰረታዊ ህጎች ተፈፃሚ የሚያደርግ እድል ያለው በመሆኑ ነባራዊ ሁኔታን ታሳቢ ያደረገ ፍትህ እንዲሰጥ ያግዛል ይላል፡፡

ይህ በአሜሪካን የነበረው የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል መርህ ከኢትዮጵያ ታሪክ፤ ከኢትዮጵያ የፌዴራል ሃገረ መንግስት አመሰራረት፤ ግንባታ እና አጠቃላይ ዓላማ አንፃር መፈተሽ እና የህግ አውጪውን ሃሳብ እና ዓላማ ማወቅ ጠቃሚ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የፌዴራል የመንግስት ሥርዓት የተመሰረተው ቀድሞ እራሳቸውን ችለው በነበሩ እና የጋራ ሃገራዊ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዓላማዎች ባልነበራቸው የተለያዩ ግዛቶች ሳይሆን ለብዙ ዘመናት በአንድ ሃገር ስር በነበሩ ከልዩነት ይልቅ አንድነቱ በጠነከረ መሰረት ላይ በተገነባ ሃገር ነው፡፡

የፌዴራል ሥርዓቱ መፈጠር ዋነኛ ምክንያትና ዓላማም በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን የማንነት፣ የቋንቋ እና የእምነት ልዩነቶች ሊያስተናግድ የሚችል የፌዴራል የመንግስት ስርዓት ለመፍጠር ነው። የፌዴራል ሥርዓቱ መፈጠር አንድነትን ከማጠንከር አንፃርም በዜጎች መካከል የነበረውን ሃገራዊ አንድነት በማስቀጠል በመከባበር ላይ የተመሰረተ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመፍጠር ዓላማ ያደረገ ነው። ከዚህ ዓላማ አንፃር ሲታይ የአሜሪካ በተለያዩ ክልል ነዋሪዎች መካከል የሚነሳ ክርክርን የፌዴራል ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን እንዲሆን በሕገ መንግስት የተደነገገው ድንጋጌ ከኢትዮጵያ ልዩ የሃገረ መንግስት ግንባታ እና ታሪክ አንፃር ተፈፃሚነት ያለው አይደለም።

አብላጫው ድምፅ በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች ነዋሪ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች የመዳኘት ስልጣን ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲሰጥ ከሚያስፈልግበት ምክንያቶች መካከል አንዱ አድልዎን ለማስቀረት እንደሆነ በዚህ ዙሪያ የተጻፉ ድርሳናት እንደሚያሳዩና በተለያዩ ክልሎች ነዋሪ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮች በክልል ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር እንዲሆን ማድረግ ዜጎች በፍትሕ ስርዓቱ ላይ እምኔታ እንዲያጡ እና ፍትሕ እንዲነፈጉ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል እና በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ሰዎች መካከል የሚፈጠሩ ክርክሮች በክልል ፍርድ ቤቶች እንዲወሰኑ ስልጣን መስጠት ነጻና ገለልተኛ ፍትሕ የሚያስገኝ አይሆንም የሚል ምክንያት ቀርቧል።

ይሁን እንጂ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 79 (2) እና (3) መሰረት በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛውም የመንግስት አካል፣ ከማንኛውም ባለስልጣን ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተፅእኖ ነፃ ሆነው እንደሚሰሩ ይደነግጋል። ዳኞች የክልል ዳኞች በክልል ጉዳይ ላይ ነፃ እና ገለልተኛ ሆነው በፌዴራል ጉዳይ ላይ ገለልተኛ የማይሆኑ ከሆነ በዚህ የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ መሰረት የሚሰጡት ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ ሊሆን አይችልም። ዳኞች በሚያዩአቸው በማናቸውም ጉዳይ ላይ ከየትኛውም አይነት አድሎ ነፃ ናቸው ተብሎ ይታመናል። የሃገራችን የዳኝነት ሥርዓት ከላይ በአሜሪካ ልምድ እንዳየነው ከታሪክ እና ከሃገር አመሰራረት ጋር በተያያዘ በክልላቸው በማይኖር ተከራካሪ ወገን ላይ አድሎ ያደርጋሉ የሚለው ሃሳብ ከእኛ ሃገር የፌዴራል ሥርዓት አመሰራረትና ዓላማ አንፃር ተቀባይነት የለውም። ይልቁንም ዳኞች አድሎ እንዳያደርጉ እና ሁሉም ሰው በህግ ፊት እኩል የዳኝነት አገልግሎት እንዲገኝ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 25 ተደንግጓል። ከዚህ አንፃር በተለይም ሃገራችን ከሚትከተለው የፌዴራል ሥርዓት አንፃር በዜጎች መካከል በዘር፣ በብሄር፣ ብሄረሰብ በቀለምና በመሳሰሉት ልዩነት እንዳይደረግ

ይከለክላል። በሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ልዩነት የለም አንጂ አለ እንኳን ቢባል ልዩነቱ ሊኖር የሚችለው በክልሎች መካከል ሳይሆን በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 25 ስር የተዘረዘሩትን ምክንያቶች መሰረት ያደረጉ ናቸው።

በመሰረቱ በአንድ ክልል ነዋሪ በሆኑ በተለያየ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች መከከል በፍርድ ቤት ክርክር ሊኖር ይችላል። በተመሳሳይ ሁኔታ በተለያዩ ክልል ነዋሪ ሆነው ነገር ግን የአንድ ብሄር ወይም ብሄረሰብ አባላት መካከል የፍታቤሄር ክርክር ሊኖር ይችላል። በሃገራችን ካለው ነባራዊ ሁኔታም ብንነሳ በሁለት ክልል ነዋሪዎች መካከል ክልልን መሰረት አድርጎ አድሎ ሊኖር እንደሚችል የሚያመለክት ድንጋጌ በሕገ መንግስቱ የለም። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ አብላጫው ድምፅ ብሄርን መሰረት የደረገ አድሎ በክልል ፍርድ ቤቶች ሊፈፀም ይችላል በሚል ስጋት የቀረበው ሃሳብ የመንቀበለው አይደለም።

የፌዴራል ፍርድ ቤት የቀድሞ አዋጅ ቁጥር 25/87ም ሆነ አዲሱ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5 ንኡስ አንቀፅ 1 (ሸ) ስር የሁለት ክልሎች ወይም የአዲስ አበባ /ድሬዳዋ ከተማ ነዋሪዎች ጉዳይ በፌዴራል ፍርድ ቤት እንዲታይ የተወሰነበት የህግ መነሻ በተመለከተ በአዋጁ ረቂቅ ከተደረገው ውይይት መረዳት የሚቻለው በኢትዮጵያ የክልል ፍርድ ቤቶች አድሎ ያደርጋሉ ከሚል ሃሳብ እንዳልሆነ መረዳት ይጫላል።

አዲሱ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ 1234/2013 ላይ የተዘጋጀ ማብራሪያ ወይም ይህንን ድንጋጌ አስመልክቶ የተቀመጠ የህግ አውጪው ዝርዝር ማብራሪያ ሃሳብ የለም። የብዝሃነት የፌዴራል የዳኝነት ስልጣን መጀመሪያ የተደነገገው በቀድሞ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 እንደመሆኑ መጠን ይህ አዋጅ ሲረቀቅ የተነሱትን ሃሳቦች ማየት ጠቃሚ ነው።

የብዝሃነት የዳኝነት ስልጣን መርህ በአዋጅ ቁጥር 25/88 ረቂቅ አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 2 ላይ የተደነገገ ሲሆን በረቂቁ ላይ ውይይት ሲደረግ በቀጥታ በዚህ ድንጋጌ ላይ የተነሳ ሃሳብና አስተያየት አልነበረም። ከዚህ ድንጋጌ ጋር ተመሳሳይ በሆነው እና በረቂቁ አንቀፅ 5 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ሥልጣንን ላይ በተደረገ ውይይት ግን የሚከተሉት ሃሳቦች ተንፀባርዋል፦

በባለጉዳዮች (በፓርቲዎች) እና በወንጀል ክብደትና ወይም ቅለት በመሳሰሉት የተለያዩ ጉዳዮችን በመመስረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወንጀል ጉዳዮች ላይ

የሚኖራቸው የዳኝነት ስልጣን መጠቀሱን፤ በመሆኑም የሕጉ አቀራረፅ ያልተመቻቸበት ሁኔታ መንስኤው የፌዴራል ህግና የክልል ህግ የሚባል ግልፅ የሆነ ነገር ስለሌለ አሁን ባለንበት የእድገት ደረጃ ለዚህ ለቀረበው አዋጅ አረቃቀቅ የአቀራረቡ ዘዴ ከቀረበበት ሁኔታ የተሻለ ባለመኖሩ ነው ይላል።

በዚህ የህጉ ረቂቅ ላይ የተካሄደው ውይይት የሚያመለክተው የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን በሕገ መንግስቱ መርህ መሰረት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ያልተቻለበትን አስቸጋሪ ሁኔታ በጊዜው በማጋጠሙ ምክንያት በባለጉዳዮች እና በወንጀል ክብደትን መሰረት አድርጎ የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል የተደረገ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

የፌዴራል እና የክልል ሕገ መንግስታዊ የዳኝነት ስልጣን ክፍፍሉ የፌዴራል እና የክልል ህግ አውጪ ስልጣንን (ህግን) መሰረት ያደረገ ቢሆንም በጊዜው ግን የፌዴራል እና የክልል ህግ ስላልወጣ ይህን መርህ ተከትሎ የስልጣን ክፍፍሉን ማድረግ አለመቻሉን ያመለክታል። ከላይ በተብራራው መርህ መሰረት የዳኝነት ስልጣን ክፍፍሉ ተግባራዊ መደረግ የነበረበት የፌዴራል እና የክልል ህጎችን መሰረት አድርጎ ነው። ነገር ግን በጊዜው ይህን ማድረግ ባለመቻሉ እንደ ጊዜያዊ መፍትሄ የተከራካሪዎችን ማንነትና እና የወንጀሉን ክብደትና ቅለት መሰረት በማድረግ የዳኝነት የስልጣን ክፍፍሉ መደረጉን ማብራሪያው ያሳያል።

አዋጅ ቁጥር 25/88 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በፀደቀ ማግስት የወጣ ህግ ነው። ሕገ መንግስቱ በ1987 ዓ.ም ሲፀድቅ የፌዴራል እና የክልል ህጎች ገና ያልወጡ የፌዴራል ስርዓቱም ቢሆን ገና በጅማሮ ላይ ነበር ማለት ይቻላል። በዚህ መነሻነት በጊዜው እንደ መፍትሄ የተወሰደው የፌዴራል እና የክልል ህግ የሚለውን ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ እንዳለ ሆኖ በአዋጁ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ስልጣን ለይቶ መደንገግ አስፈላጊ ነበር። ከዚህ አንፃር የፌዴራል ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የፌዴራሉ ህግ በመሆኑ ሳይሆን ለምሳሌ የወንጀል ጉዳይን በተመለከተ የወንጀሉ ቅለት እና ክብደትን መሰረት በማድረግ የተወሰኑት የወንጀል ጉዳዮች ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲሰጡ እንደተደረገ መረዳት ይቻላል። በተመሳሳይ ባለጉዳዮችን መሰረት በማድረግም የተወሰኑት የወንጀል ጉዳዮች ለፌዴራል የዳኝነት ስልጣን የተሰጡ ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል። በአዋጁ ይህ የተደረገው ሕገ መንግስታዊ መርሁ ይህ ስለሆነ ሳይሆን በጊዜው የነበረውን ችግር ለመቅረፍ እንደ አማራጭ መፍትሄ በመጠቀም ነው።

ከዚህ በወንጀል የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል ላይ ከተደረገው ውይይት ተንስተን በሁለት የተለያዩ ክልል ነዋሪዎች መካከል የሚነሳ የፍታብሄር ክርክር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ይሆናል

የሚለው ሃሳብ እና መርህም ከዚሁ ጋር የተገናኘ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። በሁለት ክልል ነዋሪዎች መካከል የሚነሳ የፍታብሄር ክርክር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን እንዲሆን የተደረገው ከላይ ከወንጀል ጉዳይ ጋር ተያይዞ በተደረገው ውይይት መሰረት ለጊዜው ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ታስቦ እንደሆነ መደምደሚያ ላይ መድረስ ይቻላል።

ከአዋጅ 25/88 ረቂቅ ውይይት መረዳት የሚቻለውም የብዝሃነት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነነት ስልጣን ልምድ የተወሰደው ከአሜሪካ ቢሆንም መርሁ ያስፈለገበት ምክንያት ግን የአብላጫው ድምፅ የጉባኤ አባላት እንዳሉት በክልሎች መካከል ያለውን ወይም ሊኖር የሚችል አድሎን ለማስቀረት አይደለም። ይልቁንም ህጉ ሲረቀቅ (ሲወጣ) የፌዴራል እና የክልል ህጎች ስላልነበሩ ለችግሩ ጊዜያው መፍትሄ ለመስጠት ነው። ከእነዚህ አማራጮች ውስጥ አንዱ የተከራካሪዎችን ማንነት መሰረት በማድረግ የዳኝነት ስልጣን ክፍፍሉን ስለመደረጉ ነው።

የዚህ የዳኝነት ስልጣን መርህ እና ዓላማ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር መታየት አለበት። አዋጁ ሲረቀቂና ሲወጣ የነበረው አስተሳሰብ አሁን ላይ ያለው አስተሳሰብ የተለያየ ነው። ሁሉም በሚባል ደረጃ ክልሎች በርካታ የራሳቸውን ሕጎች ያወጡ ሲሆን የፌዴራል መንግስትም በርካታ የራሱን ህጎችን አውጥቷል። የክልል ፍርድ ቤቶች እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የማስፈፀም አቅምና የስልጣን ጥያቄም ሕገ መንግስታዊ መርሁን መሰረት አድርጎ መተግበር አለበት።

አዋጅ ቁጥር 25/88 ሲወጣም ሆነ ከዚያ ወዲህ በፌዴራል እና በክልል ፍርድ ቤቶች መካከል የሕገ መንግስት ጥያቄ ወይም ክርክር ባለመቅረቡ በአዋጁ በጊዜያዊነት ተደነገገው የብዝሃነት የዳኝነት ስልጣን እንደ አንድ መፍትሄ ሲተገበር ቆይቷል። ይህ መርህ ሲተገበር የቆየው ሕገ መንግስታዊ ስለሆነ ሳይሆን የፌዴራል ስርዓቱ መመስረት ማግስት የነበረውን ጊዜያዊ ችግር ለመቅረፍ ነው። አሁን በዚህ መርህ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ቀርቦበታል። ስለሆነ ከነበረው አሰራር ይልቅ ሕገ መንግስቱ የፍርድ ቤቶችን የስልጣን ክፍፍል በደነገገው መርህ መሰረት በማድረግ ለጉዳዩ እልባት ሊሰጠው ይገባል።

የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ አንቀጽ 5(1-ሸ) ድንጋጌ ከላይ በዝርዝር ከተቀመጠው የአሜሪካ ልምድ እና አሰራር የተወሰደ ነገር ግን ደግሞ ዓላማው የተለየ ቢሆንም ከአሜሪካው አቻው በሕገ መንግስታዊ መሰረቱ በጣም ይለያል። የብዛሃነት የዳኝነት ስልጣን በአሜሪካ ብቻም ሳይሆን ለምሳሌ በአውስትራሊያምና ብራዚልም ህገ መንግስታዊ መሠረት ያለው ነው። በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ግን የብዛሃነት የዳኝነት ስልጣን መርህ ግልፅ ሕገ መንግስታዊ

ድንጋጌ የለውም። ከዚህ መርህ ጋር የሚቀራረብ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌም የለም። ስለሆነም በሕገ መንግስቱ የተከራካሪ ወገኖች የመኖሪያ አድራሻ በፌደራሉ መንግስትና በክልሎች መካከል ለተደረገው የዳኝነት የስልጣን ክፍፍል እንደ መስፈርት የሚቆጠር አይደለም።

### 3. አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል 'ሸ' ሕገ መንግስታዊነትን በተመለከተ፣

ከላይ በጭብጥ አንድ እና ሁለት ስር እንደተብራራው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5(1) ሸ ስር የተደነገገው የብዝሃነት የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል ከሕገ መንግስቱ የፌዴራል ሥርዓት ዓላማ ጋር የማይሄድ፣ በቀድሞ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 እንዲገባ የተደረገው አዋጁ ሲወጣ የፌዴራል እና የክልል ህግ ስላልነበር እንደጊዜያዊ መፍትሄ የተቀመጠ እንጂ የሕገ መንግስቱ የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል መርህ በመሆኑ አይደለም። ስለሆነም ይህን መርህ አዲሱ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መደንገጉ በሕገ መንግስቱ የፌዴራል እና የክልል የዳኝነት ሥልጣን መርህን (አንቀፅ 79፣ 80 እና 81) እንዲሁም የፌዴራል እና የክልል የሕግ አውጪ አካላት የስልጣን ክፍፍል መርህን (አንቀፅ 51፣ 52 እና 55 ) ያልተከተለ ስለሆነ በሁለት ክልል ነዋሪዎች መካከል የሚነሳ ፍታብሄር ክርክር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ነው በማለት በአዋጁ የተደነገገው ድንጋጌ ኢ-ሕገ መንግስታዊ ነው።

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5(1) ሸ ድንጋጌ ኢ-ሕገ መንግስታዊ ነው ተብሎ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሊቀርብ ይገባል በማለት በኢ-ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 84 ንኡስ አንቀፅ 2 መሰረት ይህ የውሳኔ ሃሳብ በልዩነት ለምክር ቤቱ ቀርቧል።

FDRE Council of Constitutional Inquiry

## የማስማሚያ ሐሳብ

ስሜ በተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው የጉባኤ ሰብሳቢ የማስማሚያ ሐሳቤን ከዚህ በታች እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

ከላይ በዝርዝር እንደቀረበው ትርጉም የተጠየቀበት መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች፣ በክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ በክልል እና በድሬዳዋ፣ በድሬዳዋ ከተማና በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ የፍትሐብሄር ጉዳዮች ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንደሚኖራቸው በደነገገው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1)(ሸ) ላይ ነው፡፡ ለትርጉም ጥያቄው መሰረት የሆነው ተከራካሪዎች የሚከራከሩበት ጉዳይ የክልል ጉዳይ የሆኑ እንደ ቤተሰብ፣ የውርስ፣ የመሬት አስተዳደር፣ በክልሉ የተደረጉ ወይም የሚፈጸሙ ውሎች ከሆኑና ከተከራካሪዎች ውስጥ አንዱ የሌላ ክልል ወይም የተጠቀሱት ከተሞች ነዋሪ ከሆነ ጉዳዩ የክልል ጉዳይ ተብሎ ሊታይ ይገባዋል የሚለው አረዳድ ነው፡፡ በዚህ አቅጣጫ ከታየ አንድ ጉዳይ የክልል ጉዳይ የሚባለው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሕግ በየትኛው አካል የወጣ ወይም በየትኛው ሕግ አውጪ (የፌዴራል ወይም የክልል) ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆኑ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

በቀረበው የሕገ-መንግስት ጥያቄ መሰረት የአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1)(ሸ) ድንጋጌ መሰረት ያደረገው ነዋሪነት ሆኖ ሕገ-መንግስቱ ሕግ የመተርጎምን ስልጣንን ያከፋፈለው የፌዴራል እና የክልል ጉዳዮች በሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚወሰነው ሕግ በማውጣት ስልጣን ላይ ተመስርቶ ስለሆነ በዚህ አግባብ የተጠቀሰው ድንጋጌ ከሕገ-መንግስቱ ጋር ይቃረናል የሚል ነው፡፡ እዚህ ላይ መነሳት ያለበት የአዋጁ አንቀጽ 5(1)(ሸ) በራሱ የሚቆም በቀጥታ የሚቃረነው የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ ስላለ ሳይሆን ድምዳሜው "የፌዴራል ጉዳይ" ወይም "የክልል ጉዳይ" ብሎ ሕገ-መንግስቱ የለያቸውን ጉዳዮች መለያ መስፈርት ላይ የተመሰረተ ይሆናል ብሎ በመውሰዱ ነው፡፡ ሆኖም ይህ አረዳድ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ወይም ጥያቄ የማይቀርብበት አይደለም፡፡ ስለዚህ ለቀረበው ጥያቄ እልባት ለመስጠት በቅድሚያ እነዚህ ሐረጎች በሕገ-መንግስቱ ውስጥ በምን መልክ ተተረጎሙ ወይም እንዴት መተርጎም አለባቸው የሚለውን መመለስ የግድ ይላል፡፡

የሕግ መተርጎም ስልጣንን በክልልና በፌዴራል ፍ/ቤቶች መካከል ያከፋፈለው የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 በአጭሩ የሚለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፤ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በክልል ጉዳይ የበላይና

የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል ነው፡፡ ሕገ-መንግስቱ ከዚህ ያለፈ የሚነግረን ነገር ስለሌለ ትርጉም የተጠየቀበት አንቀጽ መታየት ያለበት ከነዚህ ድንጋጌዎች (ሐረጎች) ትርጉም አንጻር በመሆኑ መተርጎም ያለበት ይህ የሕገ-መንግስቱ ድንጋጌ ነው፡፡

ሕገ-መንግስቱ የፌዴራል ወይም የክልል ጉዳዮችን ለመለየት የሚያስችል መምሪያ ወይም ጠቋሚ ወይም ትርጉም ስላልያዘ ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ መስጠት የሚቻለው እነዚህን የድንጋጌውን ሐረጎች በመተርጎም ነው፡፡ በጠያቂው ፍ/ቤት እንደቀረበው የፌዴራልና የክልል የዳኝነት ስልጣን ክፍፍልን የሕግ አውጪውን ስልጣን ብቻ ተከትሎ መፍትሔ ለመስጠት የሚደረግ ሙከራ በተቃራኒ የሚነሳው ሙግት እንደተጠበቀ ሆኖ መሬት ላይ ያለውን እውነት የሚያንጸባርቅ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን የረጋውን ነባራዊ ሁኔታ የማናጋት ውጤት ሊኖረው ይችላል፡፡ ከዚህ በላይ ግን አሁን የቀረበው የትርጉም ጥያቄ በሚመራን አቅጣጫ እስከ አሁን ያልተሄደበት መሬት ላይ ያለውን እውነት የማያንጸባርቅና ብዙ ማስተካከያ የሚጠይቅ መሆኑን ወደ ጎን በመተው የሕጉን ይዘት ለመበየን የሚቻለው ከላይ እንደተመለከተው ለተጠቀሱት የሕገ መንግስቱ ሐረጎች ትርጉም በመስጠት ነው፡፡

የህግ አወጣጥ መሰረት ተደርጎ የሚድርስብት ድምዳሜ እስከ አሁን ያለውን ትግበራ እና እውነታ የማያሳይ ነው፡፡ ለማሳያነት የሚጠቀሱት የወንጀል፣ የአሰሪና ሰራተኛ እና የንግድ ሕጎች ሲሆኑ በነዚህ ሕጎች መሰረት የሚታዩ ጉዳዮች እየተስተናገዱ ያሉት የፌዴራል ጉዳዮች ሆነው ሳይሆን እንደ ክልል ጉዳዮች ነው፡፡ የፌዴራል ጉዳይ ተደርገው ቢወሰዱ ኖሮ በነዚህ ጉዳዮች ላይ የክልል የመጀመሪያ ደረጃ/የወረዳ ፍ/ቤቶች ስልጣን ሊኖራቸው ስለማይችል እስከ አሁንም ሆነ ከዚህ በኋላ የሚሰጡት ውሳኔዎች ስልጣን በሌለው አካል የተሰጡ እንደሚሆኑ ለመረዳት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(2) እና (4) የተመለከተውን ውክልና ማየት ተገቢ ነው፡፡

ትርጉም ያስፈልገዋል የተባለው የአዋጁ አንቀጽ 5(1) (ሸ) በቀጥታ የጣሰው የሕገ-መንግስት ድንጋጌ ባለመኖሩ ውጤቱ የሚወሰነው ለህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 በሚሰጠው ትርጉም ነው፡፡ በቀረበው የትርጉም ጥያቄ የተከተለው መርህ የፌዴራል ጉዳዮች የሚባሉት በፌዴራል ሕግ አውጭው አካል የወጡ ሕጎች የሚዳኙ ብቻ የሚለው አተረጓጎም እስከ አሁን ባለው የሕግ አተረጓጎምም ሆነ የዚህ ስልጣን መተግበር መሰረት እንዳላደረገው መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የተጠቀሱት ሐረጎች ባልተተረጎሙበት ሁኔታ የተጠቀሰው ድንጋጌ ኢ-ሕገ-መንግስታዊ ነው ለማለት ወይም ድንጋጌው ግልጽ ስለሆነ የሕገ-መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም የሚለውን አቋም ለመያዛ አዳጋች ነው፡፡

በድንጋጌው ላይ ጥያቄ የተነሳው በመጀመሪያ "የክልል ጉዳዮች" ምንድናቸው ለሚለው ትርጉም ከተሰጠ በኋላ በመሆኑ ይህ ደግሞ ስልጣን ባለው አካል ባልተበየነበት ሁኔታ ገገር ትርጉም በማድረግ ውጤት መስጠት ስለማይቻል ተገቢ አካሄድ ነው ተብሎ ሊወሰድ አይችልም። ከላይ በአብላጫም ሆነ በአነስተኛ ድምጽ የቀረቡት ሐሳቦች የሚያመለክቱት ሕገ-መንግስቱ በሕግ ተርጓሚ አካላት መካከል ያደረገው የስልጣን ክፍፍል ግልጽነት የጎደለውና አንድ መርሕ አስቀምጦ ለመዳኘት አስቸጋሪ መሆኑን ነው። ስለዚህ ለዚህ መፍትሄ መስጠት የሚቻለው የስልጣን ክፍፍሉን መሰረት ወይም ይህን በተመለከተ ያለውን ብዥታ ለማጥራት በሚያስችል ሁኔታ ሕገ-መንግስቱ ያሰበውን ወይም መሰረት ያደረገውን የስልጣን ክፍፍል መርህ ነቅሶ በማውጣት ብቻ ነው።

የተከራካሪ ወገኖች ማንነት ለጉዳዩ ምንም አግባብነት የለውም እንዳይባል የፌዴራል ተቋማትና የውጭ ዜጎች በፌዴራል መንግስት የተቋቋሙና የተመዘገቡ የንግድ ድርጅቶችና ማሕበሮች እና ዜግነትን በተመለከተ (አዋጅ ቁ. 1234/2013 አንቀጽ 5(1)(በ)(ረ)(ቀ)) የፌዴራል ጉዳዮች መደረጋቸው የስልጣን መነሻ የሕግ ማውጣት ስልጣን ብቻ አለመሆኑን ጠቋሚ ነው። በተጨማሪም በጉዳዮች ዓይነትም ለምሳሌ መክሰር አንቀጽ 5(1)(መ) ፣ የኢንሹራንስ ውሎች 5(1)(ነ) ተገዶ የመያዝ ሕጋዊነት ጉዳዮች የፌዴራል የሚሆኑበት ሁኔታ መኖሩን ስናይ የስልጣን ክፍፍሉ በአንድ መርህ ላይ የተመሰረተ ነው ለማለት አያስችልም። ይህም ጥያቄው የተነሳው በአዋጁ የስልጣን ክፍፍል ላይ ብቻ ባለመሆኑ በአጠቃላይ ታይቶ ውሳኔ ካልተሰጠ በስተቀር አሻሚ ነው ቢባል እንኳ አንድን ድንጋጌ ብቻ ወስዶ ትርጉም መስጠቱ የወጥነት ችግር ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የስርዓት መናጋትን የሚያስከትል በመሆኑ መፍትሔ የሚሆነው በአጠቃላይ ጉዳዮችን የፌዴራል ወይም የክልል ለማለት መስፈርት፣ መለኪያ ወይም ሚዛን በማስቀመጥ ነው። ይህም ሊሳካ የሚችለው ለነዚህ ቃላት በምንሰጠው ትርጉም በመሆኑ በተናጠል ለመተርጎም መሞከሩ ተገቢ አይደለም።